ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


# የኦሮምኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት (በሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት)


በ

አዜብ ተፈራ



ሰኔ 2016 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

# የኦሮምኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት (በሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

በ

አዜብ ተፈራ

ዋና አማካሪ፡ ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡ ማንያለው አባተ(ዶ/ር)

ሰኔ 2016 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የኦሮምኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት (በሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት) በሚል በሚል ርእስ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በአዜብ ተፈራ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና ወጥነት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል።

የፈተና ቦርድ አባላት

ዋና አማካሪ ..................................ፊርማ...............................ቀን...................

ረዳት አማካሪ……………..…………ፊርማ……………………….ቀን……………..

የውጭ ፈታኝ ...............................ፊርማ..............................ቀን....................

የውስጥ ፈታኝ…………..................ፊርማ............................ቀን......................

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩ ይህ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት የራሴ የጥናት ውጤት የሆነ፣ ከዚህ ቀደም በየትኛውም ዩኒቨርሲቲ ለመመረቂያ ጽሁፍነት ያልቀረበ፣ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ምንጮች ሁሉ በተገቢው መንገድ እውቅና ተሰጥቷቸው የቀረቡ ስለመሆናቸው በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

አዜብ ተፈራ ____________________

## ምስጋና

በመጀመሪያ ጥናቱን አስጀምሮ ላስፈፀመኝ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው፡፡

ይህንን ጥናት ከርእስ መረጣው ጀምሮ ለረዱኝ የጥናት አማካሪዎቼ ለዶ/ር ምህረት ሳዳሞ እና ለዶ/ር ማንያለው አባተ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ይህን ጥናት ሳካሄድ ፈተናዎችን በመፈተን ለተባበሩኝ የሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን፣ በፈተናው ላይ የተሳተፉ ተማሪዎችን እና የስታስቲክስ ስሌቱን በማሳየት እገዛ ላደረጉልኝ ዶ/ር መርከብ ጌታቸውን አመሰግናለሁ፡፡ በጥናት ሥራ ላይ እንድበረታ ያላሰለሰ እርዳታ ላደረገልኝ ለባለቤቴ እንዲሁም በተለይም ይህን ጥናት በማካሂድበት ወቅት ትብብር ላደረጉልኝ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ


ይዘት ገጽ

ምስጋና ........ i

ማውጫ ........ ii

የሰንጠረዥ ማውጫ ........ iv

አጠቃሎ ........ v

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 6

1.4. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ........ 6

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 7

1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 7

ምእራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት ........ 8

2.1. የንባብ ምንነት ........ 8

2.2. አንብቦ የመረዳት ምንነት ........ 10

2.3. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፈተናዎች ባህሪያት ........ 13

2.4. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ ........ 20

2.5. የንባብ ፍጥነት ምንነት ........ 21

2.6. የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ........ 23

2.7. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 25

ምእራፍ ሶስት፤ የአጠናን ዘዴ ........ 27

3.1. የጥናቱ ዘዴ ........ 27

3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች ........ 27

3.3. የናሙና አመራረጥ ........ 27

3.3.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 27

3.3.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........ 28

3.3.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 28

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 29

3.4.1. ፈተና ........ 29

3.5. የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ዘዴ ... 30
3.5.1. የመረጃ አደረጃጀት ... 30
3.5.2. የመረጃ አተናተን ዘዴ ... 31
ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና ... 32
4.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች ... 32
4.1.1 የፈተና አንድ አንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ... 33
4.1.2 የፈተና ሁለት አንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ... 35
4.1.3 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ... 36
4.2 የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድና ሁለት ዝርዝር መረጃዎች ... 38
4.2.1 የፈተና አንድ የተጠኚ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት ... 38
4.2.2 የፈተና ሁለት የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት ... 41
4.2.3 የፈተና አንድና ሁለት አማካይ የቃላት ብዛትና የማንበብ ... 43
ፍጥነት ... 43
4.3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ... 45
ፍጥነት ጋር ያለው ግንኙነት ... 45
4.4. የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ግንኙነት በፈተና አንድ ... 46
4.5 የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ግንኙነት በፈተና ሁለት ... 47
4.6 የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የማንበብ ፍጥነት ተዛምዶ ... 47
4.7. የውጤት ማብራሪያ ... 49
ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያና አስተያየት ... 52
5.1 ማጠቃለያ ... 52
5.2 አስተያየት ... 54
ዋቢዎች ... 56

# የሰንጠረዥ ማውጫ

**የሰንጠረዥ ርእስ** **ገጽ**

ሠንጠረዥ 2.1፦ የንባብ ፍጥነት ደረጃ……………………………………………………22
ሠንጠረዥ 4.1፦ የፈተና አንድ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ስርጭት ………………33
ሠንጠረዥ 4.2፦ የፈተና ሁለት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ስርጭት ………………35
ሠንጠረዥ 4.3፦ የተጠኝዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ በሁለቱ ፈተናዎች ………….37
ሠንጠረዥ 4.4፦ የፈተና አንድ የንባብ ፍጥነት ውጤት ……………………………………39
ሠንጠረዥ 4.5፦ የፈተና ሁለት የንባብ ፍጥነት ውጤት ……………………………………41
ሠንጠረዥ 4.6፡ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አማካይ የንባብ ፍጥነት የሚያሳይ መረጃ……..43
ሠንጠረዥ 4.7፦ አማካይ የተጠኚዎች አንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት……………46
ሠንጠረዥ 4.8፦ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ልኬት በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት ኮረሌሽን ………………………………………………………………..47

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ነው። ጥናቱ የተደረገው በጅማ ከተማ በሚገኘው ሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ2016 ዓ.ም. 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ነው። ጥናቱ የተሰራው በተዛምዷዊ የምርምር ንድፍ ነው። በዚህ የጥናት ዘዴ የተጠኚዎቹን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ፍጥነት ተዛምዶ ተመርምሮ ቀርቧል። በተጨማሪም የተሰበሰበው መረጃም ከጥናቱ ዓላማና መሪ ጥያቄዎች አንጻር በመጠናዊ የምርምር ዘዴ እና ገላጭ በዓይነታዊ ምርምር ስልት (ቅይጥ ዘዴ) ተተንትኗል። ሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጅማ ከተማ ከሚገኙት ስድስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በአመቺ ንሞና ዘዴን በመጠቀም ተመርጧል። የ10ኛ ክፍል ተተኳሪ ተማሪዎች ደግሞ በአላማ-ተኮር የናሙና ዘዴ ለዚህ ጥናት ተመርጠዋል። ከ305 ተማሪዎች መካከል 20% ተጠኚዎች 61 ተማሪዎች በቀላል እጣ ንሞና ዘዴ ከአምስቱ ክፍሎች አስር አስር፣ ከቀሪው ክፍል ደግሞ 11 ተጠኚዎች በረድፋዊ ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል። የተጠኚ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነት ጋር ያለውን ተዛምዶ ምንነት ለማወቅ ፈተናዎች ተሰጥተዋል። በጥናቱ ግኝት መሰረት ተጠኚዎቹ በሁለት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች አማካይ ውጤታቸው 9.02 ከ 20 ሲሆን ከተገኘው ውጤት አብዛኛዎቹ ተጠኚዎች በአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤታቸው ዝቅተኛ ነው። ስለዚህ የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ብቃት ላይ ችግር እንዳለ አመላካች ነው። አማካይ የንባብ ፍጥነት ውጤት ደግሞ ከተጠኚዎች መካከል 3 (4.92%) ከ138-96 ቃላትን በደቂቃ ያነበቡ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ 58 (95.08%) የሚሆኑት ተጠኚዎች ደግሞ ከ89-33 ቃላትን በደቂቃ አንብበዋል። በተጨማሪም የተጠኚ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነታቸው በአማካይ 51 ቃላት በደቂቃ ሲሆን ከአማካዩ በታች ያነበቡ ተማሪዎች ደግሞ 26 (42.62%) ናቸው። ስለዚህ በጥናቱ መሰረት አብዛኛው የኢአፍ-ፈት ቋንቋ ተጠኚ ተማሪ ከፍ ያለ የንባብ ፍጥነት ችግር እንዳለበት ጠቋሚ ነው። የተጠኚዎቹ አማካይ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች እና የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች አማካይ መካከል ያለው ተዛምዶ በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት ኮረሌሽን የስሌት ቀመር ዝቅተኛ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ (-0.371252**) ሆኗል። በአጠቃላይ ኢአፍ-ፈት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነት ጋር ያለው ተዛምዶ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ከጥናቱ ውጤቶች መረዳት ተችሏል። ስለዚህ ይህ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል በማለት አጥኚዋ የመፍትሄ ሃሳቦች አቅርባለች።

# ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ከተግባቦት ክሂሎች መካከል የማንበብ ክሂል አንዱ ነው፡፡ በቋንቋ መማር ማስተማር ተማሪዎች ከሚማሩት አራቱ የቋንቋ ችሎታዎች ማለትም ከማዳመጥ፣ ከመናገር እና ከመፃፍ በተጨማሪ አንዱ ማንበብ ነው፡፡ ነገር ግን ከሁሉም የቋንቋ ክሂሎች መካከል ማንበብ አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸውም ማንበብ በመማር የሚገኝ መልእክት መቀበያ ክሂል ነዉ፡፡

ስለማንበብ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን አስቀምጠዋል፡፡ ለምሳሌ Nuttal (2000፡2) ማንበብ በፀሐፊው አእምሮ እና በአንባቢው አእምሮ መካከል ያለው መስተጋብር ውጤት ነው ይላል፡፡ አንባቢው መልእክቱን ወይም የታሰበውን ትርጉም ከጸሐፊው ለማግኘት እንዴት እንደሚሞክር የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ አንባቢው በጸሐፊው በአንባቢው የታሰቡትን ትርጉሞች ለመፍጠር ይሞክራል፣ አንባቢው መልእክቱን እና የጸሐፊውን ትርጉም ማግኘት ይችላል ማለት ነው፡፡ Alderson (2000: 28) ደግሞ ንባብ አስደሳች፣ ጠንካራ፣ ግላዊ ስራ ሲሆን አንባቢዎች በጣም የሚደሰቱበት እና ሙሉ በሙሉ ንባብን ሊቀበሉ የሚችሉት መሆኑን ገልጿል፡፡ ማንበብ ከታተመ ፅሁፍ ትርጉም ማውጣት እና ይህንን መረጃ በአግባቡ መተርጎም መቻል ነው Grabe and stroller (2011:3)፡፡ ከላይ ካለው ማብራሪያ በመነሳት ማንበብ ማለት ፅሁፍን በመመርመር ትርጉም የመሳል ችሎታን የሚፈልግ ሂደት ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ስለዚህ ማንበብ መረጃውን ከታተመ ሚዲያ የማግኘት አንዱ ሂደት ነው ማለት ነው፡፡ David (2005: 1) በበኩላቸዉ ማንበብ ጸሀፊዉ በስራዉ ያሰፈረዉን ቁምነገር ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነዉ፡፡ አንባቢዉ በንባብ ሂደት የጽሁፉን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት፤ መረጃን ከዉስጥ ለይቶ ለማዉጣት፤ የጸሐፊዉን (የደራሲዉን) ሀሳብ ይመረምራል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ማንበብ አንባቢው የሚያነበው በዓላማ እንደሆነና መረጃዎችን ለማግኘት፣ ለጠቅላላ እውቀት እና በክፍል ውስጥ ቋንቋን ለማስተማር አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም የተማሪውን ንቁ ተሳትፎ እና ፀሀፊው ያሰፈረውን ቁም

ነገር መረዳትን የሚጠይቅ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። በሌላ አነጋገር ማንበብ አንባቢው የጽሑፉን ስውር እና ግልጽ ትርጉም የመረዳት ችሎታ ነው።

አንብቦ መረዳትን በሚመለከት ደግሞ Pang (2003፡14) እንዲህ ይላሉ። አንብቦ መረዳት የቃላትን፣ ዓረፍተ ነገሮችን እና የአንድ ጽሑፍ ትርጉም የመስጠት ሂደት ነው። በሌላ በኩል እንደ Klingner (2007፡2) አባባል አንብቦ መረዳት "በርካታ ውስብስብ ሂደቶችን በማስተባበር ማለትም የቃላት ንባብ ፣የቃላት እና የአለም እውቀት እና የንባብ ቅልጥፍና ሂደት የሚያካትት እና ትርጉም መገንባትን የሚመለከት ነው።" ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚያሳየው ቃላትን መተርጎም፣ በፅሁፍ ውስጥ የተሰጡትን ሀሳቦች ትርጉሙን እና በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት የመረዳት ችሎታ ያመለክታል። Harmer (2011: 273) ደግሞ ማንበብ 'ተማሪዎችን ሳያቋርጡ እንዲያነቡ ማድረግ' ነው ይላሉ። ይህ ማለት አንባቢዎች የንግግሩን ዥረት መውሰድ እና ለዝርዝሮቹ ብዙ ሳይጨነቁ ዋናውን ነገር መረዳት ይችላሉ ማለት ነው። በሌላ አነጋገር McNamara (2007: xi, 4) አንብቦ መረዳት ቃላቶችን ከመለየት በላይ የመሄድ ችሎታን፣ ሃሳቦችን እና በፅሁፍ ውስጥ በሚተላለፉ ሃሳቦች መካከል ያለውን ግንኙነት የመረዳት ችሎታን ያመለክታል ይላሉ። በተጨማሪም አንብቦ መረዳትን ሲገልፁ ሁልጊዜ ጥረት አልባ እና ፈጣን አይደለም። ጀማሪ አንባቢዎች በእርግጥ በተናጥል ቃላት ላይ ሲታገሉ የማንበብ ሁኔታው ቀርፋፋ እና ወደማቆም ሊሄድ  እና ጥልቅ የመረዳት ደረጃዎች በእጅጉ ሊጎዱ ይችላሉ። ጥልቀት የሌላቸው አንባቢዎች ደግሞ የይዘት ቃላቶችን መለየት ከቻሉ እና አብዛኛዎቹን ዓረፍተ ነገሮች መረዳት ከቻሉ በበቂ ሁኔታ ጽሑፍን እንደተረዱ ያምናሉ። ነገር ግን ጥልቅ አንብቦ መረዳት ግምቶችን፣ ሃሳቦችን በአንድነት ማገናኘት፣ የትክክለኛነት ጥያቄዎችን በወሳኝ አቋም መመርመር እና አንዳንድ ጊዜ የደራሲያንን ተነሳሽነት መረዳትን ይጠይቃል በማለት ይገልጻሉ።

ከላይ ከተዘረዘሩት ፍቺዎች በመነሳት አንብቦ መረዳት በጽሑፍ ውስጥ የተገለፀውን የጸሐፊውን ሀሳብ የማግኘት ችሎታ ነው። የአንብቦ መረዳት ዋናው ነገር በጸሐፊው የተሰጡ ሁሉንም መረጃዎች መረዳት ነው። ይኸውም የሚያመለክተው በፅሁፍ ውስጥ ሀሳቦችን እና በፅሁፍ ውስጥ በሚተላለፉ ሃሳቦች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን መረዳት ያመለክታል። በአጠቃላይ አንብቦ መረዳት ማለት አንድን ጽሑፍ የመረዳት ችሎታ፣

መረጃውን መተንተን እና ጸሐፊው ያሰፈረውን በትክክል መተርጎም ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት በተመለከተ ትምህርት ሚኒስቴር (2007፣7) የስልጠና ማንዋል ላይ እንደገለፀው፡-

> በኢትዮጵያ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለማዳረስ ስኬታማ ስራ ቢሰራም በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን የሚማሩ ተማሪዎች የንባብ ችሎታ ግን አስደንጋጭ መሆኑን Early Grade Reading Assessment (EGRA, 2010) ጥናት ውጤት አመልክቷል፡፡ EGRA ጥናት የዝቅተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ምዘና ጥናት በስምንት የአገሪቱ ክልሎች የተካሔደ መሆኑን ጠቅሶ ባካሄደው ጥናትም 7 ቁልፍ ዘርፎችን ገምግሟል፡፡ ግምገማው ያተኮረው በ2ኛና በ3ኛ ክፍል የፊደላትን የመለየት እውቀት፣የንግግር ድምጾች ግንዛቤ፣ የፊደልና የድምፅ ግንኙነት እውቀት፣ ተዘውታሪ ቃላትንና አዳዲስ ቃላትን ማንበብ፣ ድምጽ በማሰማት አቀላጥፎ የማንበብ ግንዛቤና አዳምጦ የመረዳት ችሎታ ናቸው፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው 2ኛ ክፍልን ካጠናቀቁ ተማሪዎች መካከል 34% አንድም ቃል ማንበብ ያልቻሉ ሲሆን፣ የ3ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ ተማሪዎች መካከል 20% የሚሆኑት ምንም ቃል ማንበብ ያልቻሉ ሲሆን 30% ደግሞ በአንብቦ መረዳት ምዘና ምንም ውጤት እንዳላስመዘገቡ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ተዘውታሪ ቃላትን በማንበብ ረገድም የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች በደቂቃ 20 ቃላትን ፣ የ3ኛ ክፍል በደቂቃ 29.4 ቃላትን ማንበብ መቻላቸውን ጥናቱ አመላክቷል፡፡

ከዚህ ጥናት መረዳት የሚቻለው 2ኛ እና 3ኛ ክፍል ያጠናቀቁ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ዝቅተኛና አሳሳቢ ደረጃ ላይ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ መኖሩን በጥናት ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት የ10ኛ ክፍል በኦሮምኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ለመፈተሽ ትኩረት ይሰጣል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ንባብ ዋና ዓላማው ጽሁፍን አንብቦ መረዳት ነው፡፡ ይኸውም በአንባቢ እና በጸሐፊው መካከል የሚደረግ መስተጋብርም ነው፡፡ ጽሑፉ ደራሲው አንባቢው በተወሰኑ መንገዶች እንዲረዳው የሚፈልገውን መረጃ ያቀርባል፡፡ ስለዚህ ደራሲው በጽሑፍ ለማስተላለፍ ያሰቡትን ለመረዳት እናነባለን፡፡ ማንበብ መረዳትን እንደሚመለከት ለመጠቆም አንዱ

ምክንያት በማንበብ ውስጥ የተካተቱት ሁሉም የግንዛቤ ሂደቶች ከዚህ መሰረታዊ ግብ ጋር የተገናኙ መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ ነው። Grabe W. and Yamashita J. (2022:17)።

እንደ Ruddell (1999:37) አገላለፅ በጣም የተለመደው የአካዳሚክ የማንበብ ግብ መረዳት ነው፣ እሱም የትርጓሜ ግንባታው ጸሐፊው ካሰበው ትርጉም ጋር በተወሰነ መልኩ የሚስማማ ነው። በክፍል ውስጥ ማንበብ ሶስት ተጨማሪ ግቦች አሉት፤ መማር ማለትም የተማሪዎችን የትምህርት እውቀት ማስፋፋት፣ የማንበብ ክህሎትን ማሳደግ፣ ይህም ተማሪዎች የተሻሉ አንባቢ እንዲሆኑ እና በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ ፈታኝ የሆኑ ጽሑፎችን እንዲወጡ ለመርዳት ነው። ይህም ተማሪዎች ፅሁፎችን በማንበብ የተማሩትን በመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ክፍሎች በሙሉ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለመርዳት ነው። ስለዚህ ከላይ የተገለጸው የሚያሳየው የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ዓላማ የተሰጣቸውን ምንባብ ስለምን እንደሆነና የማንበብ ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ነው። ይኸውም በክፍል ደረጃቸው መሰረት አንብቦ መረዳታቸውን ለመለየት ነው።

ተማሪዎች በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ አንብበው መረዳት ይኖርባቸዋል። ነገር ግን አንብበው መረዳት ካልቻሉ በትምህርት ውጤታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል። እዚህ ላይ እንደ Dymoc (2005:162) አገላለፅ ተማሪዎች ከንባብ ጋር ሳይተዋወቁ፣ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን የሚጨርሱት ጥሩ የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ሳይኖራቸዉ ነው። ስለዚህ በርካታ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸዉ ደካማ ነዉ። ይኸውም ተማሪዎች የሚማሩትን አንብበው የመረዳት አቅም ስለማይኖራቸው እና የሚያነቡትን ምንባብ በጥልቀት እንዳያዩ ከማድረግ ባሻገር በትምህርት ውጤታቸው ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል። ስለዚህ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ደካማ መሆኑን እና ይኸውም በውጤታቸው ላይ የራሱ የሆነ ተፅእኖ እንዳለው ነው። ስለዚህ የዚህ ጥናትም አንዱ ትኩረት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለመረዳት ነው። በተጨማሪም እንደ ተስፋዬ (1986፣9) አመለካከት በመማሪያ መጽሀፍቱ ዉስጥ ያሉት አብዛኞቹ መልመጃዎችም የሚያተኩሩት በአንብቦ መረዳት ላይ ነዉ ቢባልም የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ይጠቁማሉ። ከላይ ከተገለፀው የምሁራኑ ምልከታ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚጨርሱት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ሳይኖራቸውና ውጤታቸውም

ደካማ ሆኖ ነው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎች መፃህፍት አብዛኛዎቹ መልመጃዎች አንብቦ መረዳት ላይ ቢያተኩሩም የአንብቦ መረዳታቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለዚህ የተገለፁት ነገሮች በተማሪዎች አንብቦ መረዳት አንፃር ስለመኖራቸው የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶ መጠናት አለበት፡፡

በቋንቋ ትምህርት ላይ አንደኛው ክሂል አንብቦ መረዳት እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በርካታ ጥናቶች እንዳሳዩት በሀገራችን ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ደካማ ደረጃ ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ ተሾመ (1997) "በከንባታ ጠንባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት" በሚል ርዕስ  እንዲሁም አያሌው (2001) "በአማርኛ ቋንቋ የፍጥነት ንባብ ክሂል ከአንብቦ የመረዳት ክሂል ጋር ያለው ተዛምዶ በወልደያ የከፍተኛ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች" ላይ በሚል ርዕስ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት ጥናት መሰረት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነና እንዲሁም የተማሪዎች የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑንና አሁንም ትልቅ ችግር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ዝቅተኛ ደረጃ መሆኑ ችግርና አሳሳቢ መሆኑን መውሰድ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ከላይ የተገለፁት ጥናቶች እንዳስቀመጡት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ በዚህ ጥናትም በኦሮምኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት እና የንባብ ፍጥነታቸውን ተዛምዶ ለመፈተሽና ያለበትን ደረጃ ለመገንዘብ እና የንባብ ፍጥነታቸውን ተዛምዶ ለመፈተሽና ያለበትን ደረጃ ለመገንዘብ ነው፡፡

የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ በተለያዩ ጊዜያት በመምህራን፣ በወላጆች፣ በተማሪዎችና በተለያዩ አጥኚዎች ተገልጿል፡፡ እንደ ምክንያትነት የሚገለፁት የተመደበው ክፍለ ጊዜ አናሳ መሆን፣ የሚነበበው ጽሁፍ ሳቢና ተመጣጣኝ አለመሆን፣ የተማሪ ቁጥር መብዛትና የመምህሩ አተገባበር አደናቃፊነት ናቸው፡፡ ስለዚህ የተጠቀሱት ችግሮች በተለያዩ ጥናቶች ቢነሱም አሁንም ችግሩ ሙሉ በሙሉ ያልተቀረፈ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡

ከላይ በተገለፀው መሰረት በችግሩ ዙሪያ ጥናት ማካሄዱ አስፈላጊነቱ የጎላ ስለሆነና ችግሮቹ ምን እንደሆኑ ለይቶ ለማወቅ የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ዝምድና ምን እንደሚመስል ጥናት አካሂዶ ማረጋገጥ ለመማር ማስተማሩ ሂደት

ውጤታማነት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አስፈላጊ ጉዳይ በመሆኑ አጥኚዋ ይህን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳት ምክንያት ነው። ለአስራ አምስት አመታት ባስተማረችበት ጊዜ ዉስጥ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ፈተናን ሲፈተኑ ብዙዉን ጊዜ የፈተናዉን የንባብ ክሂል ሳይሰሩት የመቅረት እና ቢሰሩት እንኳ ዉጤቱ ዝቅተኛ መሆኑን ታዝባለች። በተጨማሪም አጥኚዋ ከሌሎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በተማሪዎች ዉጤት ዙሪያ ዉይይት በምታደርግበትበት ጊዜ ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ፣ በቤት ስራ እንዲሁም በፈተናዎች ላይ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸዉ ዝቅተኛ እንደሆነ መምህራኑ ቢገልጹም ይህ የሆነበት ምክንያት ከምን አንጻር እንደሆነ አጥጋቢ ምላሽ እንደሌላቸዉ አስተዉላለች። ችግሩ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ከተማሪዎች የሰዓት አጠቃቀም ጋር ሊያያዝ ይችላል የሚል ግምት አላት። ስለዚህ ከምሁራን ሀሳብና በሥራ ከተገኘው ልምድ በመነሳት መንስኤውን ለማወቅና አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ምን ያህል እንደሆነ በጥናት አስደግፎ መፈተሽ ውጤቱን ያመላክታል ከሚል እምነት በዚህ ርዕስ ጥናት ለማካሄድ ያነሳሷት ምክንያቶች ናቸው።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታን እና የንባብ ፍጥነትን ተዛምዶ መፈተሽ ይሆናል። በንዑስነት ደግሞ የሚከተሉት ዝርዝር ንዑስ ዓላማዎች አሉት፤

- በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ የሚገኝበትን ደረጃ መመርመር
- በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ፍጥነትን መመርመር
- በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነት ጋር ያለውን ዝምድና መመርመር

## 1.4. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይጠበቃል።

1. በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ይገኛል?

2. በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ፍጥነታቸው ምን ይመስላል?
3. በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነትጋር ያለው ግንኙነት ምን ያህል ነው?

## 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ብዙ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል። ከሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች መካከል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል መምህራን ምን እገዛ ማድረግ እንዳለባቸው አቅጣጫ ያሳያል፤ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ይጠቁማል፤ በዚህ ርእስ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ አካላት እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል፤ በተጨማሪም ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን የሚያዳብሩበትን መንገድ ያመላክታል ተብሎ ይታሰባል።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነትን ተዛምዶ መመርመር ይሆናል። ጥናቱ የሚካሄደዉ በኦሮሚያ ክልል ጅማ ከተማ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ሞሌ መንደራ) የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ነዉ። በመሆኑም ጥናቱ የንባብ ክሂል ትምህርት ትግበራን፣ የንባብ ክሂል የማስማተር ስነዘዴን፣ የንባብ ክሂል ማስተማሪያነት የሚዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን አይመለከትም። እንዲሁም ጥናቱ ንባብ ከስርዓተ ትምህርት ጋር ያለውን አተገባበርን አይመለከትም።

# ምእራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የንባብ ምንነት

ንባብ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መማር ካለባቸው አራቱ ክህሎት መካከል መሆኑ ይታወቃል። ተማሪዎች በጥልቀት ሲያነቡ ከምንባቡ የተወሰነ መረጃን ማግኘት ይችላሉ። እንደ Pang (2003፡6) አባባል ንባብ የተጻፉ ጽሑፎችን መረዳትን ይገለጻል። በሌላ በኩል ደግሞ Grabe and Stoller (2011: xvi) ንባብ ከጽሑፍ መረጃን ለማግኘት እና የመረጃው ትርጓሜ የሚወጣበት ዘዴ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ይላሉ። ይሁን እንጂ ይህ 'ፍቺ' ስናነብ ስለሚሆነው ነገር እና አንድን ጽሑፍ እንዴት እንደምንረዳው ብዙም አያሳየንም። Nunan (2003: 68) ደግሞ ንባብን ሲገልፁ አንባቢዎች ከጽሁፉ የተገኙ መረጃዎችን እና የራሳቸውን የእውቀት ዳራ በማዋሃድ ትርጉምን ለማጎልበት የሚፈፅሙት ሂደት ነው ይላሉ። ስለዚህ በምሁራኑ ገለፃ መሰረት ንባብ ማለት በአንባቢ እውቀት በመጠቀም በቃላት እና በአረፍተ ነገር ውስጥ በታተሙ ወይም በጽሑፍ ማቴሪያሎች ውስጥ ያለውን ትርጉም ለማወቅ ሀሳብን እንደ ማስተላለፍ ሂደት ሊገለጽ ይችላል። በማንበብ ሂደት ተማሪዎች በጽሁፉ ውስጥ ስላለው መረጃ መረዳት ይችላሉ በማለት ይገልፃሉ።

ቀልጣፋ አንባቢዎች እንደመሆናችን መጠን ብዙ አይነት ጽሑፎችን እናነባለን፣ አንዳንዶቹ አውቀን ልናነባቸው ያሰብናቸው፣ እና አንዳንዶቹን በአጋጣሚ የምናገኛቸው የሚመስሉ ናቸው። በዘመናዊ ማህበረሰቦች ውስጥ ቀኑን ሙሉ እናነባለን ምክንያቱም ህትመት በዙሪያችን ስላለ እና እኛ ከምናውቀው በላይ በብዙ መንገዶች እንጠቀማለን። ቀን ቀን መጽሔቶችን ዘና ብለንም ሆነ አንዳንድ ቢሮ ውስጥ ተራ እየጠበቅን እናነባለን (Grabe W. and Yamashita J. (2022:6)።

አንድ ሰው ሊያነብ ሲነሳ የራሱ ዓላማዎች አሉት። እንደ Grabe and Stoller (2011:5) አገላለፅ ማንበብ ስንጀምር የምንወስናቸው በርካታ የመነሻ ውሳኔዎች አሉን፣ አብዛኛውን ጊዜ እነዚህን ውሳኔዎች በጣም በፍጥነት እንወስናለን ይኸውም አብዛኛውን ጊዜ ሳናውቀው ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ጋዜጣን ብንወስድ አብዛኛውን ጊዜ የፊት ገፁን በከፊል መረጃ ለማግኘት እናነባለን። ነገር ግን ጋዜጣውን በፍጥነት ለመረዳትም ግብ ይዘን እናነባለን ምክንያቱም ጥቂት ሰዎች እያንዳንዱን የጋዜጣ መስመር ለማንበብ የሚሞክሩም ስላሉ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ማንኛውም ንባብ የራሱ ምክንያት እንዳለው ነው።

ማንበብ ካለንበት የስራ ሁኔታና መቼት ጋር የተቆራኘ መሆኑን ብዙ ምሁራን ያስገነዝባሉ። ለምሳሌ Grabe and Yamashita (2022:6) ይበልጥ መደበኛ በሆኑ መቼቶች እንደ አካዳሚክ አውዶች ወይም በሥራ ቦታ አካባቢ የመማር ማስተማር ወይም በስራችን ላይ ለመሳተፍ እንድናነብ እንጠብቃለን:: ብዙዎቻችን በትምህርት፣ በሙያ እና በሙያ ደረጃ በጣም ንባብን የሚጠይቅ ሁኔታ ውስጥ እንሳተፋለን:: በእነዚህ የኋለኞቹ መቼቶች ትልቅ ትምህርት ይገኛል፤ የዚህ የመማሪያ ሁኔታ መረጃ ሰጪ ጽሑፎችን ከምንሳተፍባቸው ተግባራት እና ካስቀመጥናቸው (ከተቀመጡልን) ግቦች ጋር በተጣጣመ መልኩ ማንበብ እና መተርጎምን ይጠይቃል። እነዚህ መቼቶች ብዙ ጊዜ ከጽሁፎች ውስጥ መረጃን እንድንዋሃድ፣ እንድንተረጉም፣ እንድንገመግም እና እንድንመርጥ ያስፈልጉናል በማለት ይገልፃሉ።

በተለምዶ አካዳሚክ ወይም በሙያ መቼቶች አካባቢ አንዳንድ ጊዜ መረጃዎችን ከበርካታ የንባብ ምንጮች፣ የተለያዩ የረዥም እና ውስብስብ ፅሁፎች፣ ከስድ ፅሁፍ እና አጃቢ ስዕላዊ መግለጫ መረጃዎችን እናወጣለን:: እንዲህ ዓይነቱ ንባብ አጠቃላይ መረዳት ከመፈለግ ወይም ከግርፍ ንባብ ፈጽሞ የተለየ ነው Grabe and Stoller (2011:5)።

በንባብ ውስጥ ዋናው የንባብ ቁም ነገር ጸሀፊዎቹ ለአንባቢያን ለማስተላለፍ የሚፈልጓቸውን መልእክት ወይም ሃሳቦች መረዳት ነው (Wijaya 2018:78):: ይህ ማለት የንባብ ዋና ዓላማዎች በንባብ ጽሑፍ ውስጥ ያለውን መረጃ ማግኘት ነው:: ተማሪዎች ያንን መረጃ መረዳት ካልቻሉ ራሱን የማንበብ ዋና ነጥብ ማግኘት ይሳናቸዋል::

የምናነበው ለተለያዩ ዓላማዎች ነው። የንባብ ላይ ግንዛቤ ዓይነቶች ለአንባቢ በተሰጡት አጠቃላይ የንባብ ግቦች ይወሰናል። የተለመዱ የንባብ ግቦች የሚባሉት ለማጥናት ማንበብ፣ ለመዝናኛ ማንበብ እና መረጃን ለመፈለግ ማንበብን ያካትታሉ። ይበልጥ የተወሰኑ ተግባራትን በተመለከተ ንባብ እንዲሁ ይለያያል። ለምሳሌ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ውስጥ አዲስ ይዘት ለመማር ማንበብ፣ ለፈተና ማጥናትን፣ የተወሰኑ ጥያቄዎችን ለመመለስ፣ አጭር የምላሽ ወረቀት ለመጻፍ ወይም አቋምን የሚደግፉ ክርክሮችን መለየትን ሊያካትት ይችላል:: እያንዳንዳቸው እነዚህ የተወሰኑ ተግባራት፣ እንዲሁም እነዚህን ተግባራት ተዛማጅ የሚያደርጉ ቅንጅቶች በተወሰነ ደረጃ ወደ ተለያዩ የንባብ ሂደቶች ሊመሩ ይችላሉ Grabe and Yamashita (2022:9)። ስለዚህ ከላይ ከቀረበው ገለፃ መረዳት የሚቻለው አንድን

ፅሁፍ የምናነበው የራሳችን ግብ አስቀምጠን መሆኑንና በርእሰ ጉዳዮቹ ላይ በማጠንጠን ነው።

## 2.2. አንብቦ የመረዳት ምንነት

የአንብቦ መረዳት ምንነትን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ሀሳብ ሰንዝረዋል። እንደ Yaman, I. & Cakici, D. (2013: 373-74) የአንብቦ መረዳት ችሎታ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አስፈላጊ ክፍል ነው። ንባብ በዓላማው የመረጃ ምንጭ እና አስደሳች እንቅስቃሴ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎችን የቋንቋ እውቀታቸውን እንዲያሰፉ እና እንዲያጠናክሩ ስለሚረዳ በቋንቋ ክፍል ውስጥ በጣም ጉልህ ከሆኑ ተግባራት አንዱ ነው።

እንደ Oakhill, Cain, and Elbro (2015:1) አባባል ደግሞ አንብቦ መረዳት ብዙ የተለያዩ የግንዛቤ ክህሎቶችን እና ችሎታዎችን ማስተባበር የሚፈልግ ውስብስብ ተግባር ነው። ጽሑፍን ለመረዳት ብቻ ሳይሆን በትምህርት፣ በሥራ ላይ ስኬት እና ለማህበራዊ ህይወታችንም ይህም በኢሜል፣ በጽሁፍ እና በማህበራዊ ትስስር ገፆች ምክንያት ጠቃሚ ነው። በተጨማሪ ማንበብ የተለያዩ ፅሁፎችን ለመረዳት ያገለግላል። እንደ Snowling, Hulme, and Nation (2022፡239) ጽሑፎችን የማንበብ እና የመረዳት ችሎታ ለሁሉም የሕይወታችን ገጽታዎች (ሥራ፣ ትምህርት፣ በህብረተሰብ ውስጥ ለመሳተፍ፣ ለዕለት ተዕለት ኑሮ እና ደስታ) አስፈላጊ ነው። ይኸውም ውስብስብ ችሎታ እንደሆነ ማየት ይቻላል።

በሌላ በኩል Sadoski (2004፡76) ስለ አንብቦ መረዳት ሲገልፁ እንዲህ ብለዋል። አንብቦ መረዳት አስፈላጊ ነው። የአንባቢው እና የሕትመቱ ግብአት በአንፃራዊነት የተመጣጠነበት ቀጣይነት ያለው ነጥብ መሃል ላይ ነው። በዚህ አጋጣሚ ህትመቱ የመልእክቱን ዝርዝር ሁኔታ ለመረዳት ወሳኝ ነው። ነገር ግን የአንባቢው የፅሁፉ ግምትም እንዲሁ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ከላይ ከተገለጹት የምሁራን ሀሳብ አንብቦ መረዳት ማለት የፅሁፉን መልእክት መረዳትና የሚፈለገውን መረጃ ከአንድ ጽሑፍ ውስጥ ፈልቅቆ ማውጣትን የሚያሳይ ነው። የፅሁፉን ዋና ሀሳብ ምንነት አንባቢው ከሚያነሳቸው ፅሁፎች ላይ መገመት እንደሚገባው መረዳት ይቻላል።

አንብቦ መረዳት ዋና ተልእኮው ከሚሰጠን ፅሁፍ ላይ የምንፈልገውን ነገር ማውጣትን ይመለከታል፡፡ እንደ Snow, C. (2002፡11) አባባል አንብቦ መረዳት ከጽሑፍ ቋንቋ ጋር በመግባባት እና በመሳተፍ ትርጉምን በአንድ ጊዜ ማውጣት እና የመገንባት ሂደት ነው፡፡ አንብቦ መረዳትን ለመወሰን የጽሑፉን አስፈላጊነት እና በቂ አለመሆን ለማጉላት የምንጠቀመው የማውጣት እና የማነጽ ቃላቶችን ነው፡፡ አንብቦ መረዳት ሶስት አካላትን ያካትታል፡፡ እነሱም አንብቦ እየተረዳ ያለው አንባቢ፣ የምንረዳው ጽሑፍ እና የመረዳት አካል የሆነው ተግባር፡፡ አንባቢን ግምት ውስጥ በማስገባት አንድ ሰው በንባብ ሥራ ላይ የሚያመጣቸውን ሁሉንም ችሎታዎች፣ እውቀቶች እና ልምዶችን እናካትታለን፡፡ በሌላ በኩል Elleman and Oslund (2019፡4) አንብቦ መረዳት ማለት በአንባቢ፣ በጽሑፍ እና በተግባር ባህሪዎች መካከል ያለው መስተጋብር ነው ይላሉ፡፡ አንድ ሰው ጽሁፉ ግልጽ ሊሆንለት የሚችለው ቀላል እና ስራው ቀላል ሲሆንለት ነው (ለምሳሌ የምርጫ ጥያቄዎችን መመለስ)፣ ነገር ግን በማይታወቅ ርዕስ ላይ ውስብስብ ጽሑፍ ሲያጋጥመው ተመሳሳይ አንባቢ ሊቸገር ይችላል፡፡

አንድ ሰው ንባብን ካለ ዓላማ አያካሄድም፡፡ የተወሰነ እና አንድን ዓላማ ለማሳካት የሚካሄድ ነው፡፡ እንደ Snowling, Hulme, and Nation (2022፡239) አባባል የንባብ አውዶች እና የንባብ ግቦች የተለያዩ ቢሆኑም፣ ሁሉም ከምናነበው ነገር ትርጉም ያለው እና ወጥ የሆነ የአዕምሮ ውክልና በተሳካ ሁኔታ እንድንገነባ ይጠይቃሉ፡፡ ይህ የትርጓሜ ግንባታ አንብቦ መረዳት ነው፣ አንባቢዎች ሃሳብን ማንፀባረቅን፣ ግምገማን፣ መማርን እና የግል ትርጓሜን በሚያካትቱ ጥልቅ ዳሰሳዎች ውስጥ እንዲሳተፉ መነሻ ነው፡፡

በዚህ ላይ ማረው (2003፣108-109) ጽሁፎች በጣም ብዙ እንደሆኑና የምናነብበት ስልትም የተለያየ እንደሆነ አስቀምጧል፡፡ በአንድ መጽሄት ላይ ያለ መጣጥፍ እና ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ያለ ማስታወቂያ የምናነብባቸው ብልሃቶች ተመሳሳይ አይሆኑም ይላሉ፡፡ መጣጥፉን ስናነብ ዝርዝር የሆኑ ሃሳቦችን ለማግኘት በጥልቀት የንባብ ስልትን ስንጠቀም ሆኖም ግን ማስታወቂያዎችን ግን ስናነብ አስፈላጊ ሃሳቦችን በመለየት አላስፈላጊ ሃሳቦችን የሚያስቀር የማንበብ ዘዴን እንተገብራለን፡፡ ከምሁሩ ገለፃ መረዳት የሚቻለው የተለያዩ ፅሁፎችን

ለማንበብ የተለያዩ የማንበቢያ ስልቶችን በመጠቀም ነው፡፡ ምክንያቱም የምናነብበት ዓላማ የተለያየ ስለሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል ማረው (2003፣110) ማንበብ ክሂልን ለማስተማር የቀለለ እንዳልሆነ ይገልፃሉ፡፡ መምህሩ ከስራ ውጪ የሚሆንበት አጋጣሚ ተማሪዎች እያንዳንዳቸው በተናጥልና በአርምሞ በሚያነቡበት ጊዜ ነው፡፡ በተማሪውና በመምህሩ መካከል የንግግር መስተጋብር አይኖርም፡፡ ነገር ግን መምህሩ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸውን ለማሳደግ እንዴት መርዳት እንዳለበት ማሰብ ይኖርበታል ይላሉ፡፡

የአካዳሚክ ንባብ ተማሪዎች ጽሁፎችን በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ ለመርዳት የታሰበ ነው፡፡ Ruddell (1999:37) እንደሚለው በጣም የተለመደው የአካዳሚክ የማንበብ ግብ መረዳት ነው፣ እሱም የትርጓሜ ግንባታው ጸሐፊው ካሰበው ትርጉም ጋር በተወሰነ መልኩ የሚስማማ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ ማንበብ ሶስት ተጨማሪ ግቦች አሉት፤ መማር ማለትም የተማሪዎችን የትምህርት እውቀት ማስፋፋት፣ የማንበብ ክህሎትን ማሳደግ፣ ይህም ተማሪዎች የተሻሉ አንባቢ እንዲሆኑ እና በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ ፈታኝ የሆኑ ጽሑፎችን እንዲወጡ (እንዲያነቡ) ለመርዳት ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች ፅሁፎችን በማንበብ የተማሩትን በመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ክፍሎች በሙሉ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለመርዳት ነው፡፡ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ በመነሳት ማንበብ የራሱ የሆኑ ዓላማዎች እንዳሉት መረዳት ይቻላል፡፡ ማንበብ ተማሪዎች በምንባቡ ሊተላልፍ የተፈለገዉን መልእክት ለመገንዘብ፣ ለመረዳት፣ የሚያስችል ክሂል ነዉ፡፡ ይህም የማንበብ ትምህርት ምን ያህል ትኩረት ሊሰጠዉ እንደሚገባ ያመላክታል፡፡

Carrell (2006፡12) በበኩላቸው ደግሞ ማንበብ ውስብስብ አእምሯዊ ሂደት የሚንጸባረቅበት በጽሀፊ የቀረበን ጽሁፍ ሀሳብ (ስሜት) ለመለየት፣ ለመገንዘብ (ለመረዳት)፣ ለመተርጎምና ለመተንተን፣ አካላዊ አእምሯዊ እና ስሜታዊ ጉዳዮችን ያካተተ መስተጋብራዊ ሂደት ነው ብለውታል፡፡ ስለዚህ ከላይ የቀረበው ብያኔ የሚያሳየው ማንበብ የፀሐፊውን ሃሳብ ማስተዋል፣ መለየት፣ መተርጎም እና መተንተን የሚጠይቅ ውስብስብ አካላዊ፣ አእምሯዊ እና ስሜታዊ መስተጋብር ነው፡፡

እንደ Nuttall (2000:49) እና ማረው (2003፣109-110) አገላለፅ ዋናዎቹ የንባብ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው::

1.የአሰሳ ንባብ (Skimming)፡- የጽሑፉን ፍሬ ነገር ለማግኘት/ለመጨበጥ በፍጥነት ስለምን እንደሚያወራ ለማወቅ የሚደረግ የንባብ ስልት ነው፡፡

2. የምልከታ ንባብ (Scanning)፡- የተወሰነ መረጃ ለማግኘትና ለይቶ ለመረዳት በፍጥነት የሚከወን ንባብ።

3. ሰፊ ንባብ (Extensive Reading)፡- ረዘም ያሉ ጽሑፎችን ማንበብ፣ ብዙውን ጊዜ የሚነበበው ለራስ ደስታ ሲሆን ንባቡ ሰፊ በመሆኑ አጠቃላይ ግንዛቤ ለመጨበጥ እንዲቻል በንቃት የሚከወን ነው።

4. ጥልቅ ንባብ (Intensive Reading)፡- አጠር ያሉ ጽሑፎችን ማንበብ፣ የተለየ መረጃ በጥልቀት ለማውጣት ሲባል በዝርዝርና በጥልቀት የሚከወን ንባብን የሚያካትት ነው። ይህ ዓይነት ንባብ ከፍጥነት ይልቅ ጥልቀትን መሰረት የሚያደርግ ነው።

እንደ በድሉ (1996፣28) አገላለጽ ተማሪዎች በዝምታ የሚያነቡበት ሁኔታ ህይወታዊ ነው ይላሉ። ይኸውም በዚህ ዘዴ ተማሪው በራሱ ፍጥነት ያለማንም ጣልቃ ገብነት ወይም እርዳታ በራሱ ፍጥነት ያነባል። በዚህ ምክንያት ነው የንባቡ ዘዴ ህይወታዊ ነው የሚባለው። ከመማሪያ ክፍል ውጭ ባለው ሁኔታ ተማሪው በአብዛኛው የሚጠቀመው የዝምታ ንባብን ነው። ለምሳሌ ጋዜጦች፣ መፃህፍት፣ ደብዳቤዎች፣ ማስታወቂያዎች ድምፅ በማሰማት አይነበቡም። የዚህ የዝምታ ንባብ ዘዴ ሌላው ጥቅሙ ተማሪው ያልተረዳውንና ያስቸገረውን አረፍተ ነገር ወይም አንቀፅ  ደግሞ ደጋግሞ ማንበብ መቻሉ እና በራሱ ፍጥነት ስለሚያነብ ነው። ከላይ በተገለፀው መሰረት የዝምታ ንባብ ምንም ጣልቃገብነት ስለማይኖርበትና በአንባቢው ፍጥነት ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ ህይወታዊ ነው።

## 2.3. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፈተናዎች ባህሪያት

የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመለካት የተለያዩ አይነት ፈተናዎችን መጠቀም ይኖርብናል። እንደ Alderson (2000:205-206) እና Arshad, A., Shakir, A. and Ahmad, M. (2020:254) አገላለፅ አንብቦ  መረዳት ሊለካ የሚችለው በተለያዩ ጥያቄ ዓይነቶች መሆኑን ይገልፃሉ። ለምሳሌ የምርጫ ጥያቄዎች፣ የአጭር መልስ ጥያቄዎች፣አዛምድ እና እውነት ወይም ሐሰት… ናቸው። McNamara (2007፡110-111) ደግሞ በብዙ የትምህርት አውድ ውስጥ፣ የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ግምገማ ብዙውን ጊዜ የሚገመተው ከትክክለኛው ንባብ በኋላ የሚቀርቡ ባለብዙ ምርጫ ጥያቄዎችን በመሳሰሉ መለኪያዎች ላይ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች በተለምዶ የሚመለሱት ከጽሑፎቹ የመጀመሪያ ንባብ በኋላ መሆኑን አጽንዖት መስጠት አስፈላጊ ነው ይኸውም በማንበብ ጊዜ ሂደቶችን በቀጥታ ከመገምገም በተቃራኒ መሆኑ

ነው። አንብቦ መረዳት በጽሑፉ ባህሪያት እና አንባቢዎች ወደ ንባብ ሁኔታ በሚያመጡት መካከል ውስብስብ መስተጋብር ውጤት ነው።

አንብቦ መረዳትን ለመለካት ብዙ መንገዶች አሉ:: የአንብቦ መረዳትን ለመገምገም አንዳንድ የተለመዱ መንገዶች አሉ። እነሱም ማጠቃለያ፣ ክፍት የሆኑ ጥያቄዎች እና የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው። "ዝግ" ሥራ የሚባለው ምንባብ ወይም አንድ ዓረፍተ ነገር የሚጨምር ሲሆን ተማሪው ባዶ ቦታውን መሙላት ወይም ትክክለኛውን ቃል ከምርጫዎች መምረጥ እንዳለበት የሚያሳይ ነው። ማጠቃለያ ደግሞ ተማሪው የታሪኩን ዋና ሀሳብ በራሱ ቃላቶች ማስቀመጥን ያካትታል። ለሁለቱም ክፍት እና ለምርጫ ጥያቄዎች ተማሪው ምንባቡን ያነባል እና ከዚያ በይዘቱ ላይ ተጨባጭ ወይም የግመታ ጥያቄዎችን ይጠየቃል Hendricks (2013፡8)። ከላይ እንደቀረበው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት ዋናው መሳሪያ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ነው።

እነዚህ የተመረጡት ምንባቦች ባላቸው አመቺነት እና ከአንድ በላይ የሆኑና በቂ መረጃዎችን በውስጣቸው የያዙ ምንባቦችን በመጠቀም ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ምዘናውን አስተማማኝ ማድረግ ይቻላል። ምክንያቱም ከምንባብ ምንባብ የተማሪዎቹ የማንበብ ፍላጎት ሊለያይ ይችላል።

በተጨማሪም እንደ Alderson (2000:204) የምርጫ ጥያቄዎች የአንባቢዎችን የጽሁፍ ሂደት ችሎታ ለመገምገም በጣም የታወቀ አሰራር ነው። የተማሪዎችን አስተሳሰብ ለማነቃቃት የምርጫ ጥያቄዎችን መጠቀም እንደሚቻል ይገልጻል። ይኸውም አራቱ አማራጮች ወይም 'አስጨናቂዎች' አንዳቸው ከሌላው በግልጽ ካልተለዩ፣ ተማሪዎች ትክክለኛውን አማራጭ ለመምረጥ የተወሰነ ስሜት ማሳየት አለባቸው። Kong (2019፡52) በበኩሉ በተለያዩ የቋንቋ ፈተና እና ግምገማ የምርጫ ጥያቄ ቀዳሚ ነው። ለፈተና አውጪዎች ብዙውን ጊዜ ለትልልቅ ፈተናዎች ተመራጭ ነው ይኸውም በከፍተኛ ደረጃ አስተማማኝ ስለሆነ ነው ይላል። እንደ ምሁራኑ አባባል ከሌሎች የፈተና ዓይነቶች የምርጫ ጥያቄዎች የተሻሉ መሆናቸውን ይገልፃሉ። ምክንያቱም ተፈታኞች ያነበቡትን ምንባብ ምን ያህል እንደተረዱ ለመለየት ስለሚያስችል ነው።

ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ እውነት/ሐሰት ፈተናዎች በክፍል ፈተናዎች ውስጥ ለመካተት ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው ምክንያቱም ከበርካታ የምርጫ ፈተና ጥያቄዎች በተለየ መልኩ

በቀላሉ እና በፍጥነት ሊዘጋጁ ስለሚችሉ መምህሩ ለሌሎች ስራዎች ተጨማሪ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያስችላቸዋል፡፡ Alderson (2000:211) ይህን ዓይነት ፈተና ለማውጣት ቀላል ነው ይላሉ፡፡ ይኸውም ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተማሪዎች ከሁለት አንዱን መምረጥ ያካትታል፡፡ ይህ ተማሪዎች "በመገመት" ብቻ ትክክለኛ መልሶችን የመስጠት እድሉ ከፍተኛ በመሆኑ ይተቻል፡፡ እውነት/ሐሰት ፈተና ግን ሁለት ዋና ጉዳቶች አሉት፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የማግኘት 50% ዕድል አላቸው፡፡

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት ሲታሰብ ምን ዓይነት ጥያቄዎች መሆን አለበት የሚለው ይታሰባል፡፡ የምርጫ ጥያቄዎችና አጭር መልስ የሚሹ ክፍት ጥያቄዎች ዋነኛ የአንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚለኩ እንደሆኑ Stavanas and Oded (1993: 481) ይገልፃሉ፡፡ እንደሚታወቀው የተለያዩ የጥያቄ ዓይነቶች የራሳቸው ደካማና ጠንካራ ጎኖች አሏቸው፡፡ ይህን በመደገፍ Weir (1990:43) እያንዳንዱ የፈተና ዓይነት የራሱ ጥንካሬና ድክመት አለው ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሌላው የጥያቄ ዓይነት ደግሞ ክፍት ጥያቄ ሲሆን አንባቢዎች በመልሳቸው ሳይገደቡ የሚመልሱት ነው፡፡ ስለ ክፍት ጥያቄዎች ምንነት Heaton (1989:133) ሲገልፁ 'ክፍት-ጥያቄዎች' የሚለው በተፈታኞች ላይ ሙሉ ለሙሉ ግላዊ ምላሽ የሚሰጡበትን ጥያቄዎች ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ የሚፈለገው ምላሽ ከአንድ ቃል መልስ እስከ አንድ ወይም ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ሊደርስ ይችላል፡፡

በጣም ሁለገብ ጥቅም ያለው የፈተና ቅርጽ የምርጫ ጥያቄ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ፈተና ከቀላል እስከ ውስብስብ የተለያዩ የትምህርት ግቦችን መለካት ይቻላል፡፡ የምርጫ ጥያቄ ሰፊ በሆነው ተፈፃሚነት እና ለሁሉም ዓይነት ይዘቶች ተስማሚነት ስላለው በብቸኝነት የሚጠቀሙበት ነው Arshad, Shakir, and Ahmad (2020:254)፡፡ እንደ ምሁራኑ አገላለፅ የምርጫ ጥያቄዎች የተለያዩ ትምህርት ይዘቶችን ለመለካት የሚረዱና ተመራጭ መሆናቸውን ነው፡፡

Williams (1984:67-68) ደግሞ አንብቦ የመረዳት ሂደትን ለመለካት የምርጫ ጥያቄዎች እጅግ ተዘውታሪና የመጀመሪያውን ስፍራ የሚይዙ ናቸው፡፡ ይህም ጥያቄዎቹ አንብቦ መረዳትን ከመለካቱ አኳያ እጅግ ውጤታማ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህ መረዳት

የሚቻለው በአጠቃላይ የምርጫ ጥያቄዎች በጣም ሰፊ ይዘቶችን ለመሸፈንና ተፈታኞች በቀላሉ እንዳይገምቱ ስለሚያደርጉ ተዘውታሪና ተመራጭ ናቸው።

በተጨማሪም እንደ Heaton (1989:117) አባባል የምርጫ ፈተና የአንብቦ መረዳትን ለመፈተሽ ጠቃሚ መንገድን ይሰጣል። ነገር ግን ሁሉም የምርጫ የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ጥሩ የአንብቦ መገንዘብ ፈተናዎች አይደሉም። ቀደም ሲል በግልጽ እንደተገለጸው በአንድ ፈተና ለመለካት ያቀዱትን ስኬት መጠን በአብዛኛው የሚመሰረተው በእያንዳንዱ ጥቅም ላይ በሚውሉት ፈተና ዓይነት ውጤታማነት ላይ ነው።

የምርጫ ጥያቄዎች የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳላቸው Williams (1984:68), Arshad, Shakir, and Ahmad (2020:254), Osterlind (2002፡163-164) እና Kong (2019፡53) እንደሚከተለው በዝርዝር አስቀምጠዋል።

### ሀ/ ጠንካራጎናቸው

ከጥቅሞቹ መካከል ዋነኛው ከሌሎች የፈተና ዓይነቶች በላይ የይዘት እና የስነ-ልቦና ሂደቶችን ለመገምገም በተጨማሪ ተለማጭ መሆኑ ነው። ተማሪዎቹ ለመስራት አይቸገሩም፤ በቀላሉና በፍጥነት ለማረም ያስችላሉ፤ ለሙከራ ያህል በቅድመ ፈተና መልክ በመስጠት የክብደታቸው ደረጃና የአዘገጃጀት ድክመታቸውንም ለመገምገም አመቺ ናቸው፤ ጥያቄዎቹን ለመመለስ ምንባቡን አንብበው ከመረዳት ውጪ የመናገርም ሆነ የጽሁፍ ችሎታን አይጠይቁም፤ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚለኩ ብቻ ሳይሆኑ አንብቦ መረዳትንም ያግዛሉ። ምክንያቱም ተፈታኙ የመልሱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከተቸገረ ምንባቡን ዳግም ሊያነብ ይችላል ይላሉ።

በሌላ በኩል በምርጫ ጥያቄ ቅርፅ የሚስተናገደው ይዘት ከሌሎች የጥያቄ ዓይነቶች የበለጠ ሊሆን ይችላል። ይኸውም ከሌሎች የጥያቄ መመለሻ ቅርፆች ይልቅ ለመገምገም ሰፊ ይዘትን ለመሸፈን ያስችላል። የምርጫ ጥያቄ አውጪዎች የተፈታኞችን የአስተሳሰብ ሂደቶች በአማራጮች እንዲቆጣጠሩ ያስችላቸዋል። ይኸውም የበለጠ የተራቀቀ የአንብቦ መረዳት አካላት (አስተያየቶችን፣ አመለካከቶችን፣ ክርክሮች እና የመሳሰሉትን) ከክፍት ምላሽ የበለጠ ቁጥጥር ባለው መንገድ መፈተን ይችላሉ።

የምርጫ ጥያቄ በጣም ሁለገብ ጥቅም ያለው የፈተና ቅርጽ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ፈተና ከቀላል እስከ ውስብስብ የተለያዩ የትምህርት ግቦችን መለካት ይቻላል፡፡ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ እንደሆነ ውስብስብ እና የተራቀቀ ግምገማን ይፈቅዳል፡፡ ጥሩ የምርጫ ጥያቄዎች ከፍተኛ የአስተሳሰብ ችሎታዎችን መገምገም ይችላሉ፡፡

### ለ/ ደካማ ጎናቸው

የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልስ ምንባቡን አንብበው ሳይረዱ በግምት ሊያገኙ ይችላሉ፤ ለማዘጋጀት ጥንቃቄና ብዙ ጊዜ ይወስዳሉ፤ ተፈታኞቹ ምንባቡን ሳይረዱ ጥያቄዎቹን በመመለስ ሊሳሳቱ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተፈታኞች ከጥቂት አማራጮች ውስጥ አንዱን እንዲመርጡ በመጠየቅ የምርጫ ጥያቄ ተፈታኞችን ፈጠራ ወይም ትክክለኛ አስተሳሰብን ከማሳየት ይከለክላል፡፡

## ክፍት ጥያቄዎች

'ክፍት- ጥያቄዎች' የሚለው ቃል በተፈታኞች ላይ ሙሉ ለሙሉ ግላዊ ምላሽ የሚሰጡትን ጥያቄዎች ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ የሚፈለገው ምላሽ ከአንድ ቃል መልስ እስከ አንድ ወይም ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ሊደርስ ይችላል Heaton (1989:130)፡፡

በተጨማሪም ክፍት ጥያቄዎች ሰፊ መልስ የሚሹ ሲሆን እንደ ተፈታኙ አረዳድ መልሶች እንዲሰጥ ይፈልጋሉ፡፡ እንደ Weir (1990:43) እና Haladyna, T. M. and Michael, C. R. (2013:147,180) አገላለፅ ክፍት ጥያቄዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት በጣም ጠቃሚ ናቸው፡፡ ነገር ግን እንደ ሌሎቹ የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተናዎች ጠንካራና ደካማ ጎን አላቸው፡፡

### ሀ) ጠንካራጎናቸው

ክፍት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጪን ሙሉ መብትና እድሎችን በመስጠት የራሳቸውን መልስ እንዲሰጡ ያደርጋሉ፡፡ ተፈታኞቹ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች በግምት ሊያገኟቸው አይችሉም፡፡

### ለ) ደካማ ጎናቸው

በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች የክፍት ጥያቄዎች እርማት ግልጽነት ይጎለዋል። ይኸውም ለትክክለኛነቱ ስጋትን ይፈጥራል። ከአንብቦ መረዳት አልፎ ሀሳብን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታን ይጠይቃል። ምናልባት ክፍት የሆኑ ጥያቄዎችን የመጠቀም በጣም አስቸጋሪው ገጽታ በመተንተን ደረጃ ላይ ይመጣል።

ከላይ ከተገለፀው መረዳት የሚቻለው የምርጫም ሆነ የክፍት ጥያቄዎች የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሏቸው። ስለዚህ የጥናቱን ውጤት አስተማማኝ ለማድረግ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመመዘን ሁለቱንም የጥያቄ አይነቶች ማካተት ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ደግሞ እንደ አለም (1995፣12-13) አገላለጽ የአንብቦ መረዳትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥያቄዎች በጽሁፍ ወይም በቃል ሊቀርቡ ይችላሉ። አቀራረባቸውም አጭር መልስ እንዲሰጡ በማድረግ፣ በክፍት አጠያየቅ፣ በምርጫ ወይም በእውነት ሐሰት በሉ በሚል መልኩ ሊሆን ይችላል። ጥያቄዎቹ የሚቀርቡበት መንገድ የተለያየ ሊሆን ቢችልም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ግን ግብ መቺ መሆን እንዲችሉ ከዚህ የሚከተለትን ነጥቦች መሰረት ሊያደርጉ ይገባል።

1. ጥያቄዎቹ ምንባቡን ያላነበበ ሰው ሊመልሱ የሚችሉ ሊሆን አይገባም።

2. ጥያቄዎቹ በአንድ በተወሰነ የምንባቡ ክፍል ላይ የተመሰረቱ ሳይሆኑ ሁሉንም የምንባቡን ክፍል በሚዳስሱበት መንገድ የሚዘጋጁበት ሁኔታ ሊመረመር ይገባል።

3. የጥያቄዎቹ ቁጥር እጅግም ሳይበዛ እጅግም ሳያንስ በቂ የሆነ መጠን እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

4. የተለያዩ የአንብቦ መረዳት መልመጃ የማቅረቢያ መንገዶች አሉ። ስለዚህ ጥያቄዎቹን በተለያየ አቀራረብ መንገድ ለማቅረብ መሞከር አስፈላጊ ይሆናል።

5. ጥያቄዎቹ አንድ አንባቢ ሊኖረው ከሚገባው የንባብ ስትራቴጂ ጋር የማስተዋወቅ ባህል ሊኖራቸው ይገባል።

6. ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ ምንባቡን በበለጠ እንዲረዱ የሚያግዙ መሆን ይኖርባቸዋል።

7. ጥያቄዎቹ የተገለጹበት ቋንቋ ከምንባቡ ቋንቋ የጠነከረ ወይም የከበደ መሆን አይኖርበትም፡፡

8. የጥያቄዎቹ መልሶች ተማሪው በደረጃው ሊኖረው ከሚገባው የቋንቋ ብቃት የሚልቅ የቋንቋ አጠቃቀም መጠየቅ የለባቸውም፡፡

9. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የተማሪውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍ ሊያደርጉ በሚችሉበት መንገድ እንጂ የተማሪውን ችሎታ የሚፈትኑ ዓይነት ሆነው መቅረብ አይኖርባቸውም፡፡

10. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምረውና ተቀናጅተው የሚቀርቡበትን መንገድ ማፈላለግ አስፈሊጊ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ስለ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነት እና ጠንካራ ደካማ ጎናቸው ተገልጿል፡፡ Hughes (2003:136) የንባብ ችሎታን መፈተሽ ከንግግር ችሎታ ፈተና ጋር ሲወዳደር አታላይ ይመስላል በማለት ይገልፁታል፡፡ ምንባብ ወስደው ስለሱ አንዳንድ ጥያቄዎችን ሲጠይቁ እርሶም እዚያው አሉ፡፡ ነገር ግን የንባብ ሙከራን በፍጥነት ማውጣት መቻልዎ እውነት ቢሆንም፣ በጣም ጥሩ ፈተና ላይሆን ይችላል ስለዚህ እርስዎ እንዲለካው የሚፈልጉትን አይለካም ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ክሂሎችን በሁለት ጎራ በመመደብ የፈተና አወጣጡንም ለማየት የሞከሩ ምሁራን አሉ፡፡ ለምሳሌ Hughes (2003:136) ዋናው ችግር የኢፍሉቅ ክህሎት (receptive skills) መለማመድ የግድ ወይም አብዛኛውን ጊዜ እራሱን በግልፅ ባህሪ ውስጥ የሚገለጥ አለመሆኑ ነው፡፡ ሰዎች ሲጽፉ እና ሲናገሩ እናያለን፣ እንሰማለን፤ ሲያነቡ እና ሲያዳምጡ ብዙውን ጊዜ የሚከታተሉት አይደሉም፡፡ የቋንቋ ፈታኙ ፈተና እጩው የማንበብ (ወይም የማዳመጥ) ችሎታዎችን እንዲለማመድ ብቻ ሳይሆን እነዚያን ችሎታዎች በተሳካ ሁኔታ መጠቀምን የሚያሳዩ ተግባራትን ማዘጋጀት ነው ፡፡

የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ላይ Grellet (1981:9) የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ከመገንባት በስተጀርባ ያለው ሀሳብ የተለያዩ እና ተለዋዋጭ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ ሁሉም የመልመጃ ዓይነቶች በተፈጥሯቸው ጠቃሚ ወይም የማይጠቅሙ አይደሉም በአንድ የተወሰነ ጽሑፍ ላይ ሊተገበሩ ይችሉ

ይሆናሉ። ለንባብ የሚረዱ ተግባራት ለሚነበቡ ጽሑፎች እና ለአንባቢው ተነሳሽነት ተስማሚ መሆን አለባቸው። ጽሑፉን ሙሉ በሙሉ ለመረዳት የጸሐፊውን ዓላማ፣ አመለካከት እና ቃና ማጤን ያስፈልጋል። ክፍት፣ ባለብዙ ምርጫ፣ ትክክል ወይም ስህተት እና ሌሎች የጥያቄ ዓይነቶች ይህንን ለመሸፈን ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪ የመልመጃዎቹ ዓላማ በግልፅ መገለጽ እና በማስተማር እና በፈተና መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት መደረግ አለበት። የሙከራ ፈተና የበለጠ ትክክለኛነትን የሚመስሉ ልምምዶችን የሚያካትት ሲሆን በማስተማር ግን ክህሎቶቹን ለማዳበር መሞከር አለበት ይላሉ።

በተጨማሪም እንደ Grellet (1981:4) አባባል በእውነተኛ ህይወት የንባብ አላማችን በየጊዜው ይለያያል። ስለዚህ መልመጃዎችን በምንዘጋጅበት ጊዜ ጥያቄዎቹን እና ተግባራቶቹን እንደየተጠናው የፅሁፍ አይነት እና የማንበብ አላማ መለዋወጥ አለብን። ለምሳሌ በተመደቡ ማስታወቂያዎች ገጽ ላይ ሲሰሩ የእያንዳንዱን ማስታወቂያ ዝርዝር ግንዛቤ የሚጠይቁ ልምምዶችን ማቅረብ ተፈጥሮአዊ አይደለም። ይህም ተማሪዎቹን ተስፋ ከማስቆረጥ እና ከትክክለኛው የንባብ ዓላማቸው ጋር የተጣጣሙ የንባብ ስልቶችን እንዳያዘጋጁ ያግዳቸዋል። ከኚህ ምሁር አገላለፅ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ በፅሁፉ ዓይነት እና የንባብ ዓላማችን ላይ መመስረት ይኖርባቸዋል።

## 2.4. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ

የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ መለኪያዎች በተለያዩ ምሁራን ተዘግበዋል። ለምሳሌ Afiyah (2021:169) የአንብቦ መረዳት ውጤትን እንደሚከተለው አስቀምጠዋል። ከ80-100 በጣም ጥሩ፣ ከ66-79 ጥሩ፣ ከ56-65 መካከለኛ፣ ከ40-55 ዝቅተኛ፣ እና ከ30-39 በጣም ዝቅተኛ በማለት አስቀምጠዋል። Narayanaswamy (1975: 144) እና Nuttall (1982፡ 37) ደግሞ በአንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ላይ የአንብቦ መረዳት ችሎታው በቂ ደረጃ ነው የሚባለው የተፈታኙ ውጤት 70% ከሆነ ነው። በተጨማሪም እንደ Nation (2009:71) አባባል በጥንቃቄ የተሞላ የዝምታ ንባብ አንባቢዎች የአንብቦ መረዳት ፈተና ላይ ከአስር ሰባት ወይም ስምንት ነጥብ ማግኘት አለባቸው። ከአስር ስድስት ወይም ከዚያ በታች ያሉት ውጤቶች በጣም ዝቅተኛ እና አንባቢው ንባቡን እስኪረዳ ድረስ ቀጣይ ጽሑፎችን በተመሳሳይ ፍጥነት ማንበብ አለበት። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ጥሩ አንባቢ በፈተናው ከመቶ 70% እስከ 80% ማስመዝገብ ይኖርበታል። የተፈታኙ ውጤት ከ80% በላይ ከሆነ

በጣም ጥሩ ችሎታ ሲኖረው ውጤቱም ደግሞ 60% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ግን ችሎታው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ Kaval (1979፡27) ደግሞ በአንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ከ75%-90% ያገኘ ተማሪ አንብቦ የመረዳት ችሎታው በቂ ሲሆን፣ ተፈታኙ 90% ወይም ከዚያ በላይ ካገኘ አንብቦ የመረዳት ችሎታው ከፍተኛ እና ውጤቱ ከ75% በታች ከሆነ ግን ዝቅተኛ ነው በማለት ያስቀምጣሉ። ይኸውም ችሎታው በቂ ደረጃ ላይ ለመድረስ የተፈታኙ ውጤት ከ75% በላይ መምጣት እንዳለበት ያሳያል።

ከላይ ምሁራኑ ያስቀመጧቸውን መስፈርቶች መነሻ በማድረግ ለተማሪዎቹ በሚሰጣቸው የችሎታ መለኪያ ፈተና ውጤት መሰረት ከ90%- 100% በጣም ከፍተኛ፤ ከ70%- 89% በቂ፤ 60% እና ከዚያ በታች በጣም ዝቅተኛ ብሎ መውሰድ ይቻላል።

## 2.5. የንባብ ፍጥነት ምንነት

በ1950ዎቹ ውስጥ የአንብቦ መረዳት መፅሃፍት ለአንባቢዎች ጥቅም ላይ የዋሉት በMichael West ፅሁፎች ላይ ነው። የንባብ ፍጥነት ፍላጎት ትልቅ ቦታ ያገኘው በBell (2001:2) እንደተጠቀሰው በFry (1963) and De Leeuw & De Leeuw (1965) ፅሁፎች እ.ኤ.አ. በ1960ዎቹ ዓመታት ውስጥ ነበር። Fry እንደሚናገሩት ጥሩ አንባቢዎች በደቂቃ 350 ቃላት ሲያነቡ፣ ማእከላዊ አንባቢዎች 250 ቃላት በደቂቃ ፍጥነት ያስመዘገቡ ሲሆን የዝግታ አንባቢዎች ደግሞ በደቂቃ 150 ቃላቶችን ይደርሳሉ። De Leeuw በደቂቃ ውስጥ 230-250 ቃላትን በጥቅሉ የተጠቀሰው ለህዝብ አማካይ የመጀመሪያ ፍጥነት እንደሆነ ይጠቅሳሉ። እነዚህ ቀደምት ግንዛቤዎች የፍጥነት ንባብ ኮርሶችን በማጎልበት እና በፍጥነት እንዲያነቧቸው የሚሳቡ ግለሰቦች በወረቀት-ተኮር ቴክኒኮች በመጠቀም እና የቴክኖሎጂ እርዳታዎች በሚገኙበት ለምሳሌ ፕሮጀክተሮች ወይም የንባብ ማሽኖች እንዲያድጉ አድርገዋል።

የንባብ ፍጥነትን በተመለከተ ከተካተቱት በጣም ጠንካራ እና ቀደምት ግኝቶች መካከል በዝምታ ማንበብ፣ ከቃል ንባብ በፍጥነት እና በማስተዋል የላቀ ነው Sadoski (2004:29)። ስለዚህ ተማሪዎች ፅሁፍን ጮክ ብለው እንዲያነቡ ከመጠየቅ ይልቅ ለንባብ ፍጥነታቸው እና ግንዛቤያቸው በዝምታ ማንበብ የተሻለ ነው። በፀጥታ በማንበብ የተማሪዎችን ትኩረት በዋናነት የፅሁፉን ፍሬ ነገር ለመረዳት በአይን እንቅስቃሴ ላይ እንጂ ሌላውን እንቅስቃሴ

እንደ አንደበት እና አፍ እንቅስቃሴ አለማተኮር ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም፣ እንደ ጥሩ አንባቢዎች፣ ደካማ አንባቢዎች ሙሉ ትኩረታቸው ከንባብ በመማር ላይ እንዲያተኩር የመግለጽ፣ የቃላት ንባብ እና የቅልጥፍና ችሎታዎች የላቸውም (Klinger, Vaughn, & Boardman, 2007፡4)።

እንደ Fry (2011፡12) የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነት ደረጃ ለመለካት ከዚህ በታች ያለውን በሰንጠረዥ ውስጥ የተቀመጠውን አብነት በማድረግ መጠቀም ይቻላል። ይኸውም ንባቡ 500 ቃላት ያሉት መሆን ይኖርበታል። የንባብ ደረጃ መለኪያ ከዚህ በታች ተቀምጧል።

**ሠንጠረዥ 2.1፡- የንባብ ፍጥነት ደረጃ**

| ሰከንድ | ደረጃ |
|---|---|
| 45 ሰከንዶችና በታች | በጣም ፈጣን |
| 46-60 ሰከንዶች | ፈጣን |
| 61-90 ሰከንዶች | ማእከላዊ ከፍተኛ |
| 91-119 ሰከንዶች | ማእከላዊ |
| 120-150 ሰከንዶች | ዝቅተኛ |
| 150 ሰከንዶችን ከዚያ በላይ | በጣም ዝቅተኛ |

ምንጭ፡- Fry (2011፡12)

በሌላ በኩል ደግሞ እንደ Nation (2009: 62-63) አባባል አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት አንድ የተዋጣለት አንባቢ በአፍ መፍቻ ቋንቋው አማካይ የንባብ ፍጥነት ከ250 እስከ 300 ቃላት በደቂቃ መሆን አለበት:: ነገር ግን በ L2 ወይም በኢአፍ-ፊት ቋንቋ ይህ አማካይ ንባብ ከ200-250 ቃላት በደቂቃ ይወርዳል::

የንባብ ክህሎት አስፈላጊ ገጽታ ፍጥነት ነው። እሱም አንድ ሰው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በትክክል ማንበብ የሚችለውን የቃላት ብዛትን ያመለክታል። ይህ ፍጥነት እንደ የንባብ

አይነቱ ይለያያል። Fry (1975) በMora, Quito, and Macías (2021:12) ላይ ሶስት ደረጃዎችን ይጠቁማሉ። እነሱም ተራ ንባብ (መጽሔቶች፣ መጽሃፎች እና ቀላል ጽሑፎች) ሲያጠቃልሉ ከ250-500 ቃላት በደቂቃ በ70% የመረዳት ደረጃ፣ የጥናት ንባብ (ጥልቅ ትኩረትን የሚጠይቁ ውስብስብ ጽሑፎች) ከ180-200 ቃላት በደቂቃ በ90% መረዳት እና ከላይ ላዩን ንባብ (የፅሁፍ ዳሰሳ) ከ800 ቃላት በደቂቃ ከ50% መረዳት ጋር ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ Windi, Nasriandi and Syahrir (2023፡1007) የንባብ ፍጥነትን ቃላትን በደቂቃ ደረጃውን እንደሚከተለው አስቀምጠዋል። ዝግተኛ አንባቢዎች ከ50-100 ቃላት በደቂቃ፣ አማካይ (መካከለኛ) አንባቢዎች 100-200 ቃላት በደቂቃ እና ከአማካይ በላይ የሆኑ አንባቢዎች ደግሞ 300-400 ቃላትን በደቂቃ ያነባሉ። ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን በተለየ ሁኔታ የንባብ ፍጥነት ቃላት በደቂቃ የWindi, Nasriandi and Syahrir (2023፡1007) ዝቅ ያለና ተአማኒነት ያለው ይመስላል።

### 2.6. የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ

አንብቦ መረዳት ከንባብ ፍጥነት ጋር የተዛመዱ እንደሆኑ ምሁራን ይገልጻሉ። ለምሳሌ Fry (2011፡15) በአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት መካከል ያለው ተዛምዶ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ገልፀዋል። ይኸውም በፍጥነት ያንብቡ በትንሹ ይረዳሉ፣ በጣም ዝግ ብለን ስላነበብን ፅሁፉን አልተረዳንም ማለት አይደለም በማለት ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል። በማንበብ ፍጥነት እና በንባብ መረዳት መካከል በጣም የቅርብ ግንኙነት አለ። Mora, J. F. , Quito, I. R. and Macías, L. E. (2021፡11) ደግሞ ከላይ ከተገለፀው በተቃራኒ ንባቡ እየቀነሰ በሄደ ቁጥር የመረዳት ችሎታው እየጨመረ ይሄዳል። ሌሎች ጥናቶች እንደሚያሳዩት አንድ ሰው ከፍተኛ የአንብቦ መረዳትን ካሳየ የማንበብ ፍጥነቱም ከፍተኛ ሊሆን ይችላል ይላሉ።

እንደ Ostrov (2002፡8) አገላለፅ ደግሞ አንባቢው ምን ያህል በደንብ እንዳነበቡ በሁለት ነገሮች ላይ የተመሰረተ ነው። የመጀመሪያው ፍጥነት እና ሁለተኛው መረዳት ነው። በጣም በፍጥነት ካነበቡ ነገር ግን ፅሁፉን መረዳት ካልቻሉ ምናልባትም አላነበቡትም ማለት ነው ይላሉ። የንባብ ፍጥነት ብዙውን ጊዜ የሚለካው የተነበቡት የቃላት ብዛት በደቂቃ ነው። የእርስዎ ቃላት ብዛት በደቂቃ በእውነቱ ለብዙ ደቂቃዎች የሚቆይ የንባብ ፈተና ላይ በአንድ ደቂቃ ውስጥ የሚያነቡት አማካይ የቃላት ብዛት ነው። ነገር ግን ይህ ምን ያህል በፍጥነት እንደሚያነቡ ሀሳብ ለማግኘት ብቸኛው መንገድ አይደለም።

Wainwright (2007፡34) ደግሞ የመረዳት እና የንባብ ፍጥነት ሁለት የተለያዩ ክፍሎች ሳይሆኑ የአንድ ሂደት ሁለት ባህሪያት መሆናቸውን ማስታወስ አስፈላጊ ነው። የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ መረዳት ጋር እንደሚገናኝ ግልጽ ነው። ሁለቱም የማንበብ ግንዛቤ ደረጃ እና አጠቃላይ የንባብ ጥራትን ይመለከታል ቢባል ትንሽ ግራ የሚያጋባ ይሆናል። "የማንበብ ፍጥነት" እና "መረዳት" የሚሉት ቃላቶች አመቺ እንዲሆን ጥቅም ላይ ይውላሉ። ነገር ግን ሁልጊዜ እርስ በእርሳቸው ተመሳሳይ ተጽእኖ እንደማይኖራቸው ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። እንደሚታወቀው ለምሳሌ ቀርፋፋ የንባብ ፍጥነቶች ሁልጊዜ ወደ ተሻለ ግንዛቤ አይተረጎሙም ወይም ፈጣን ፍጥነቶች ወደ መጥፎ ግንዛቤ ሊተረጎሙ አይችሉም ይላሉ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው አንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት አስፈላጊ ነገር ግን አንድ አይነት አለመሆናቸውና ነገር ግን የሚገናኙ እንደሆነ ነው።

በሌላ በኩል ሊመረመር የሚገባው ነገር በማንበብ ፍጥነት እና በአንብቦ መረዳት መካከል ያለው ግንኙነት ነው። በአጠቃላይ ሁለቱ በቅርብ የተቆራኙ እንደሆኑ ክርክሮች አሉ። የሁለቱ ተዛምዶ ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ ሲያወዛግብ ኖሯል። ሁለቱም ነፃ ሆነው ወይም ተዛምደው የሚገኙ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን እንደሚታሰበው በጣም ቀርፋፋ አንባቢ መልእክቱን በጥቂቱ ሊረዳ ይችላል Bell (2001፡2)። ከዚህ በተጨማሪ Fraser (2004: 135, 137) ደግሞ የንባብ ፍጥነት እና አንብቦ መረዳት ሲጣመሩ ዋና የንባብ ክሂል ሁለት ወሳኝ ክፍሎች ናቸው። ጠቀሜታው የአንባቢዎችን የንባብ ቅልጥፍና መጠን በመወሰን ላይ ባለው ሚና ላይ ነው። ዝቅተኛ ንባብ ኢአፍ-ፊት ቋንቋ ተማሪዎች ያነበቡትን ውጤታማ እና ቀልጣፋ ግንዛቤ እንዳያገኙ እና የሚፈለገውን የንባብ መጠን እንዳያስተናግዱ ያግዳቸዋል። ስለዚህ ኢአፍ-ፊት ቋንቋ ተማሪዎች የማንበብ ቅልጥፍናን ማሻሻል ለአስተማሪዎች ዋና ግብ ነው።

በተጨማሪም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ አንብቦ ከመረዳት ጋር ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት ሊኖራቸው ይገባል። ማንበብ ዓላማው እንዴት ማንበብ እንዳለበት የሚወስን ቢሆንም፣ ተማሪው በተቻለ መጠን ፍጥነት ባለው ሁኔታ ጽሑፍ ለማንበብ መሞከር አለበት። ይህ የሆነበት ምክንያት ያለ ፍጥነት እና/ወይም የመረዳት ችሎታ የሌለው ግንዛቤ ተቀባይነት ስለሌለው ነው። በሌላ አነጋገር ፍጥነት እና አንብቦ መረዳት የማይነጣጠሉ ናቸው። Nuttall (1982፡33) የንባብ ፍጥነት እና አንብቦ መረዳት በቅርበት የተሳሰሩ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። ሁለቱም አንብቦ መረዳት እና ፍጥነት አስፈላጊ እና

የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ ከላይ የቀረቡት ትንታኔዎች የሚያመለክቱት የንባብ ፍጥነትና አንብቦ መረዳት የሚያያዙ መሆናቸውን ነው፡፡ እንደ Nuttall (1996፡58) አመለካከት አንድ አንባቢ 70% ነጥብ ያለው እና 200 ቃላት በደቂቃ ቢያስመዘግብ 100% ውጤት ካለው እና 140 ቃላት በደቂቃ ፍጥነት ካለው የተሻለ አንባቢ ነው፡፡ ስለዚህ የአንብቦ መረዳት ነጥብ 70% የተሻለ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው አንብቦ መረዳት ከፍጥነት ጋር ለተማሪዎች አካዳሚያዊ ስኬት አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸውም ንባብ በመማር ማስተማር ላይ ዋና ነገር በመሆኑ ነው፡፡

ስለዚህ ማንበብ የሰው ልጅ መረጃ የሚያገኝበት አንዱ እንደሆነና የማንበብ ልምድ የሚያዳብርበት እንዲሁም የሚጠቅመውን ወይም ሊጠቅም የሚችለውን እየመረጠ ማንበብ እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.7. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኚዋ በአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ዙሪያ የተሰሩትን ጥናቶች ለመመልከት ሞክራለች፡፡ በአገራችን በአማርኛ ቋንቋ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በርካታ የሀገራችን ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ደካማ እንደሆነ ነው፡፡ ተስፋዬ (2001) የሚያመላክቱት የተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን ነዉ፡፡

አያሌው (2001) በአማርኛ ቋንቋ የፍጥነት ንባብ ክሂል ከአንብቦ የመረዳት ክሂል ጋር ያለው ተዛምዶ በወልዲያ የከፍተኛ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተመሰረተ ጥናት በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ባደረጉት ጥናት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ጥናቱ የተደረገበት ቦታ፣ ጊዜና የክፍል ደረጃው 11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ መሆኑ የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህኛው ጥናት ትኩረት ያደረገው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ላይ ስለሆነ ነው፡፡

ሌላው ጥናት ደግሞ በረከት (2010) በሰገን አከባቢ ሕዝቦች በሰገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በአማርኛ ቋንቋ ኢአፍ-ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በሚል ዕርስ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በመፈተሽ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

ጥናቱም መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመባቸው ፈተና የተጠቀመ በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስለው የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች 9ኛ ክፍል መሆናቸው፣ ከ4 የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ተመርጠው የቀረቡ በመሆናቸው፣ የጥናቱ ጊዜ እና የትምህርት ቤት መገኛውም ከዚህ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በሚል ርዕስ መሰራቱ ተመሳሳይ ያደርገዋል፡፡ ይህ ጥናት ግን ትኩረት ሊያደርግ የታቀደው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ላይ ነው።

ዮሐንስ (2013) በአማርኛ ቋንቋ ኢአፍ-ፈት የሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ትንተና በጉጂ ዞን በነገሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት የሚለው ይገኝበታል። ይህ ጥናት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ትንተና ላይ ማተኮሩ የሚመሳሰል ያደርገዋል። ነገር ግን ለጥናቱ ናሙና ተማሪዎችን የመረጠው ከገጠር የመጡትን በተለየ ሆስቴል ውስጥ የሚኖሩ ኦሮምኛ ተናጋሪዎችን መሆኑ፣ የክፍል ደረጃውን ለመምረጥ የተጠቀመበት ዘዴ ደግሞ በነሲብ የናሙና ዘዴ መሆኑ እና የጥናቱ ጊዜ ከዚህ ጥናት ጋር ይለየዋል። በተጨማሪም ይህ ጥናት ደግሞ የታሰበው በጅማ ከተማ በሚገኝ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ለመስራት ማተኮሩ ደግሞ ይለየዋል።

በመጨረሻም ታሪኳ የማታ (2015) በአፋን ኦሮሞ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት (ዴዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) የሚለው የጥናት ርዕስ ከዚህ የጥናት ርዕስ ጋር እና የምርምሩ ዘዴ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም የጥናት ቦታ፣ ጊዜና የክፍል ደረጃው 10ኛ ክፍል በመሆኑ ይለያል።

ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች በተጨማሪ በርካታ ጥናቶች ቢኖሩም አሁንም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ዝቅተኛ በመሆኑ ተጨማሪ ስራዎች ይጠበቃሉ። በአጠቃላይ ጥናቶቹ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም እንኳን የሁሉም ጥናት ዓላማ የተለያየ ነው።

# ምእራፍ ሶስት፤ የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነትን ተዛምዶ መፈተሽ ይሆናል። የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ተዛምዷዊ የምርምር ስልት ጥቅም ላይ ውሏል። ስለዚህ በዚህ የጥናት ስልት ላይ በመመርኮዝ የተጠኚዎቹን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ፍጥነት ተዛምዶ ተመርምሮ ቀርቧል። በተጨማሪም የአጠናን ዘዴው መጠናዊ የምርምር ዘዴን እና ዓይነታዊ የምርምር ስልትን (ቅይጥ ዘዴ) ነው። ምክንያቱም አጥኚዋ ይህን የምርምር ዘዴ የምትጠቀምበት ምክንያት ከተማሪዎች የንባብ ፈተና የተገኘውን መረጃ በገለጻና በቁጥር (በመቶኛ) ተንትና ስለምታቀርብ ነው።

## 3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች

ጥናቱ ትኩረት ያደረገው ኦሮምኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነትን ተዛምዶ መመርመር ላይ ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች በሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው።

## 3.3. የናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት መሳካት ዋና ሚና የሚጫወቱት የሚመረጡ ናሙናዎች ናቸው። እነዚህ ናሙናዎች የትምህርት ቤት አመራረጥ፣ የክፍል አመራረጥ እና የተማሪዎች አመራረጥ ናቸው።

### 3.3.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በጅማ ከተማ ዉስጥ ካሉት ስድስት የመንግስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ት/ ቤት በአመቺ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል። እንደ ያለው (2011፡132) አባባል አመቺ ወይም የግኝት ንሞናን መጠቀም የሚቻለው ጥናት አድራጊው አመቺ የሆኑ ሰዎች ወይም ነገሮችን በቅርበት ሲያገኝ ምርምሩን ሲያካሄድ ነው ይላል። ስለዚህ አጥኚዋ የመረጃ አሰባሰቡን ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መረጃ መሰብሰብ እንዲያስችላት፣

ጥናቱን ለማካሄድ ስለሚመቻት ለምሳሌ ቅርበት፣ ለትራንስፖርት ምቹ እና ጥናቱን ለማካሄድ በቂ መረጃ ስለምታገኝ ሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን መርጣለች፡፡

### 3.3.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል በአመቺ የናሙና ዘዴ ለዚህ ጥናት ተመርጧል፡፡ ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍሎች ብሄራዊ ፈተና ላይ ስለማይሰጥ ለጥናቱ በቂ እና ትክክለኛ መረጃ ያስገኛል ተብሎ ስላልታመነ አልተመረጡም፡፡ 10ኛ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት በትምህርት ቤት ቆይታ ያላቸው መሆኑ፣ ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ይልቅ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉ የተሻሉ በመሆናቸው ለጥናቱ በቂ እና ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ፡፡ ስለዚህ ለጥናቱ ሊመረጥ ችሏል፡፡

### 3.3.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

የተማሪዎችን የናሙና አመራረጥ በተመለከተ ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤት ዉስጥ በ2016 ዓ.ም ሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከተመዘገቡ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ ተማሪዎች በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ እዚህ ላይ ያለው (2011፣ 132) ከጥናቱ ዓላማ አንፃር የዓላማ ተኮር ናሙና ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች ይመርጣል፡፡ ይኸውም እነማን ቢመረጡ የሚፈለገውን መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡ ይችላሉ ከሚለው አንፃር መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ ተዛምዷዊ ከሆነ እንደ ያለው (2011፣ 139) አገላለፅ የጥናቱ አካላይ በርካታ አባላት ከሆኑ የናሙና አባላቱ ከ30 ማነስ የለባቸውም ይላሉ፡፡ ስለዚህ ለዚህ ጥናት ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ ተማሪዎች ቁጥር 305 ሲሆን እነዚህ ተማሪዎች በስድስት መማሪያ ክፍሎች የተደለደሉ ናቸው፡፡ ከስድስቱ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ካሉት 305 ተማሪዎች መካከል 20 ፐርሰንት ተጠኚዎች ወደ ጥናቱ ቢመጡ በቂ እንደሆነ በማሰብ በቀላል እጣ ንሞና ዘዴ በማውጣጣት ለማሳተፍ ታቅዶ በዚሁ መሰረት ተከናውኗል፡፡ ለጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተመረጡት ተማሪዎች 61 ሲሆኑ በቀላል እጣ ንሞና ዘዴ ከአምስቱ መማሪያ ክፍሎች 10፣ ከቀሪ አንድ ክፍል ደግሞ 11 ተጠኚዎች በረድፋዊ ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ እነዚህን ናሙናዎች ለማግኘት በጥናቱ አካላይ ላይ የሚገኝ እያንዳንዱ ተጠኚ የመጀመሪያው ናሙና በዕጣ ተሰይሞ በእኩል ርቀት ላይ የሚገኙ ሌሎች ናሙናዎች አመጣጥኖ ለመውሰድ ረድፋዊ ንሞና ዘዴ ተወስዷል፡፡ ይህ

የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ለተጠኚ ተማሪዎች እኩል የመመረጥ እድል ስለሚሰጥና የአንዱ ተጠኚ በናሙናነት መመረጥ በሌላ የመመረጥ እድል ላይ ምንም ተጽእኖ ስለማያስከትል ነዉ።

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነትን ተዛምዶን መፈተሽ ይሆናል። በመሆኑም ለጥናቱ መሰብሰቢያነት የሚዉሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ፈተና እና የማንበብ ፍጥነት መለኪያ ፈተናዎች ናቸው።

### 3.4.1. ፈተና

ለተማሪዎች የሚሰጡ ሁለት ዓይነት የአንብቦ መረዳት እና የንባብ ፍጥነት ምንባብ ተዘጋጅተዋል። ፈተናዎቹ በአጥኚዋ ተዘጋጅተው ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪ ባላቸው መምህራን፣ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራንና በአማካሪ ከታዩ በኂላ ማስተካከያ ተደርጎባቸው እንዲፈተኑ ተደርጓል። የመጀመሪያው ምንባብ ልቦለድ ፅሁፍ ላይ ተመርኩዞ በ316 ቃላት ተጠናክሮ የቀረበ ሲሆን ሁለተኛው ምንባብ ደግሞ በመጣጥፍ ጽሁፍ ላይ ተንተርሶ 391 ቃላትን ያካተተ ሆኖ ተዘጋጅቷል። (አባሪ “1” እና “2” ይመልከቱ)።

የአንብቦ መረዳት እና የማንበብ ፍጥነት የሚገኝበትን ደረጃ ለማወቅ የሚረዳ የማንበብ ፍጥነት መለኪያ ምንባብ ለሁለት ጊዜ ቀርቦላቸዋል። የንባብ ፍጥነትን ለመለካት የNuttal (1982፡36) የንባብ ፍጥነት መለኪያ ስልት/ ሂሳባዊ ቀመር) በጥናቱ ውስጥ ተግባራዊ ተደርጓል።

የፈተና ጥያቄዎቹም በተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ላይ የተነሱትን መሰረታዊ ነጥቦችም ከግምት ዉስጥ በማስገባት ተዘጋጅተዋል። እንደ McNamara (2007:110-111) በብዙ የትምህርት አውድ ውስጥ፣ የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ግምገማ ብዙውን ጊዜ የሚገመተው ከትክክለኛው ንባብ በኂላ የሚቀርቡ ባለብዙ ምርጫ ጥያቄዎችን በመሳሰሉ መለኪያዎች ላይ ነው። በተጨማሪም Heaton (1989:117) የምርጫ ፈተና የአንብቦ መረዳትን ለመፈተሽ ጠቃሚ መንገድን ይሰጣል ይላሉ። የምርጫ ጥያቄዎቹ 20 ናቸው። ጥያቄዎቹ ከቀላል

እስከ ከፍተኛ ማሰላሰልንና በጥልቅ ንባብ ላይ የተመሰረቱ ምላሾችን የሚጠይቁ እንዲ ምንባቦቹን ሳያነቡ በግምትና በአጠቃላይ እውቀት እንዳይመልሱ አስፈላጊው ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡

ለተማሪዎች የሚሰጠው ፈተናው የንባብ ፍጥነታቸውንና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለመለካትና ያለበትን ደረጃ ለማወቅ ብሎም መፍትሔ ለመፈለግ የተዘጋጁ ሲሆኑ በራሳቸው እንዲሰሩ ገለፃ ተደርጎላቸዋል፡፡ ፈተናው በሚሰጥበት ወቅት ተማሪዎች ድምፅ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ሆኗል፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ አንብቦ የጨረሰበትን ሰአት በስም ዝርዝራቸው ላይ የጨረሱበትን ሴኮንድ ተመዝግቧል፡፡

ተፈታኞቹ በየተራ ወደ መፈተኛ ክፍል በመግባት የማንበብ ፍጥነት መረጃ ለመሰብሰብ የሚያነቡት ጽሁፍ የያዘ ወረቀት፣ የፈተና ወረቀት እና ደቂቃ መቆጣጠሪያ የሞባይል ሰአት (stop watch) አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች በሁለት ሳምንታት በየተራ በሁለት መምህራን አማካኝነት በሁለት ክፍሎች ውስጥ በአንድ ግዜ የተመረጡት ተማሪዎች እንዲያነቡና እንዲፈተኑ ሆኗል፡፡ እያንዳንዱ ተጠኚ በአንብቦ መረዳት ፈተናው ከ20 ያገኘው ውጤት ተመዝግቦ በድግግሞሽ እና በፐርሰንት ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ የንባብ ፍጥነትን በተመለከተ ደግሞ እያንዳንዱ ተጠኚ በደቂቃ ምን ያህል ቃላትን እንዳነበበ በሰንጠረዥ ተቀምጧል፡፡

## 3.5. የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ዘዴ

### 3.5.1. የመረጃ አደረጃጀት

ለዚህ ጥናት ብቁ የሚሆኑ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ከተመረጡ በኋላ በጥናቱ ዓላማ እና ምን ማድረግ እንዳለባቸው በአጥኝዋና በረዳት መምህራን አማካኝነት ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የሚዘጋጀው ፈተና የንባብ ፍጥነታቸውንና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ያለበትን ደረጃ ለማወቅ ብሎም መፍትሔ ለመፈለግ የተዘጋጀ በመሆኑ መስራት ያለባቸው በግላቸው እንዲሰሩ ተነግሯቸዋል፡፡

አጥኝዋ ከረዳት መምህራን ጋር በመሆን እያንዳንዱ ተማሪ ድምጽ ሳያሰማ እንዲያነብ ፈተናው በሚሰጥበት ወቅት ተከታትላለች፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ በምን ያህል ሴኮንድ እንዳነበበ እና አንብቦ የጨረሰበትን ሰአት የተማሪዎችን ዝርዝር በያዘው ቻርት ላይ

ተመዝግቧል። ለተማሪዎቹ የአንብቦ መረዳት ጥያቄ የያዘውን የጥያቄ ወረቀት ከመስጠቱ በፊት የፍጥነት መለኪያ ምንባብ ፈተናው ተሰብስቦ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ተደርጓል። ይኸውም ወደ ኋላ ሄደው ምንባቡን እያዩ ጥያቄዎቹን እንዳይሰሩ ታስቦ ነው። በመጨረሻም አጥኝዋና ረዳት መምህራን የተማሪዎችን ዝርዝር በመያዝ እያንዳንዱ ተማሪ ምን ያህል ቃላት በደቂቃ እንዳነበቡና ምን ያህል ጥያቄ እንደመለሱ ታርሞ ተመዝግቧል።

### 3.5.2. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጅማ ከተማ በሚገኘው ሞሌ መንደራ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ በኦሮምኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ነው። ስለሆነም በአንብቦ መረዳት ችሎታና በንባብ ፍጥነት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለማሳየት በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት ኮረሌሽን (Pearson product moment correlation) የስሌት ቀመር አማካኝነት ፍተሻ ተደርጓል። በፍተሻውም የሚገኘው ውጤት በመጠናዊና ዓይነታዊ የምርምር ስልት (ቅይጥ ዘዴ) በመጠቀም ስታትስቲካዊ ትንተና ተሰጥቶበታል። ስለዚህ መረጃዎቹ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ባላቸው ግንኙነት መሰረት ተፈትሸው ውጤቱ ተተንትኗል።

# ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና

በዚህ ምእራፍ ስር አጥኚዋ የጥናቱ ዋና አላማ የሆነውን በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነትን ተዛምዶ መፈተሽ ይሆናል። ይህ ምእራፍ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች የሚተነተንበት እና ማብራሪያ የሚሰጥበት ነው። ለዚህ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት አጥኚዋ የተጠቀመችው ዘዴ ፈተና ነው። ስለዚህ ለተጠኚ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ሁለት የተለያዩ ምንባቦች ውጤቶች ላይ ተመርኩዞ መረጃዎቹ በቁጥርና በገለፃ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል።

## 4.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች

የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነትን ለመለካት ሁለት የተለያዩ የምርጫ ጥያቄዎችን የያዙ ሁለት ምንባቦችን መሰረት ያደረጉ ናቸው። ለእያንዳንዱ ምንባብ 20 የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው እርማቱ በአጥኝዋ ከ20 ከታረሙ በኋላ ተጠኚዎቹ በየግል ያስመዘገቡት ውጤት ተመዝግበዋል። በውጤቱ ላይ በመንተራስ በሁለቱ ፈተናዎች እያንዳንዱ ተጠኚ ያስመዘገቡበት የሁለቱ ፈተናዎች አማካይ ውጤት ተመዝግቧል። አባሪ “4”ን ይመልከቱ።

ከዚህ በታች በቀረቡት ሁለት ሰንጠረዦች የተጠኚዎቹ አንብቦ የመረዳት ውጤት ስርጭት እንዲሁም አንብቦ የመረዳት ውጤት ገላጭ እስታቲስቲክስ ትንተና ቀርቧል።

## 4.1.1 የፈተና አንድ አንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት

ሠንጠረዥ4.1፡- የፈተና አንድ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ስርጭት

| የተመዘገበ ውጤት ከ20 | ድግግሞሽ (frequency) | መቶኛ (%) |
|---|---|---|
| 2 | 3 | 4.92 |
| 3 | 4 | 6.56 |
| 4 | 5 | 8.20 |
| 5 | 6 | 9.84 |
| 6 | 10 | 16.39 |
| 7 | 3 | 4.92 |
| 8 | 2 | 3.27 |
| 9 | 4 | 6.56 |
| 10 | 2 | 3.27 |
| 11 | 2 | 3.27 |
| 12 | 4 | 6.56 |
| 13 | 6 | 9.84 |
| 14 | 3 | 4.92 |
| 15 | 0 | 0 |
| 16 | 3 | 4.92 |
| 17 | 3 | 4.92 |
| 18 | 1 | 1.64 |
| 19 | 0 | 0 |
| 20 | 0 | 0 |
| ድምር | 61 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ 4.1. ላይ የቀረበው መረጃ 61 የጥናቱ ተተኳሪዎች በአንብቦ መረዳት ፈተናው ከ20 ያገኙት ውጤት ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ተመዝግቦ ቀርቧል፡፡ በአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ ተጠኚዎቹ ያስመዘገቡት ውጤት እንደሚያሳየው ዝቅተኛው ውጤት 2 ከ20 ሲሆን፣ ነገር ግን ከፍተኛው የአንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ደግሞ 18 ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው በአንብቦ መረዳት ፈተናው በዝቅተኛው እና ከፍተኛው ውጤት

መካከል የ16 ማርክ ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ በአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ በቁጥር አንጻራዊ ብዛት ባላቸው ተማሪዎች የተመዘገበ አንድ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤቶች (Mode) አለ፡፡ ከአንብቦ የመረዳት ውጤት ውስጥ (6 ከሃያ ያመጡ) ብዙ ድግግሞሽ (Mode) 10 ሲሆን ይህን ያስመዘገቡ ተማሪዎች 16.39% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

ከአጠቃላይ ተጠኚዎች ውስጥ 37 (60.66%) የሚሆኑት 9 እና ከዚያ በታች ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ 24 (39.34%) የሚሆኑት ደግሞ 10 እና ከዚያ በላይ ውጤት አምጥተዋል፡፡ ስለዚህ ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተጠኚዎች ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአንብቦ መረዳት ውጤታቸው ከሬሎቹ ተማሪዎች ማለፊያ ማርክ እና ከዚያ በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ናቸው፡፡

በአንብቦ የመረዳት ፈተና አንድ የተመዘገበው ከፍተኛ ውጤት 18 ከ20 ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት ደግሞ 2 ከ20 (ሁለት ከሃያ) ነው፡፡ የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ አማካይ ውጤ ት 8.66 ሲሆን ይኸውም የተጠኝ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑን ነው፡፡ በአንቦቦ መረዳት ፈተና አንድ መደበኛ ልይይት 4.556626 ነው፡፡ ይህንን መረጃ ከአባሪ “3” ካለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡ መደበኛ ልይይት የሚያሳየው የእ ያንዳንዱ ተጠኚ ውጤት ከአማካይ ውጤት ምን ያህል በአማካይ እንደሚርቁ ነው ያለው ( 2011፣254)፡፡ ስለዚህ በዚህ ፈተና ላይ የተጠኚዎቹ አማካይ የአንብቦ መረዳት ውጤታቸው 8.66 ሲሆን ልይይቱ በአማካይ 4.556626 ከ8.66 ይርቃል ማለት ነው፡፡

## 4.1.2 የፈተና ሁለት አንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት

**ሠንጠረዥ 4.2 የፈተና ሁለት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ስርጭት**

| የተመዘገበ ውጤት ከ20 | ድግግሞሽ (frequency) | መቶኛ (%) |
|---|---|---|
| 2 | 2 | 3.28 |
| 3 | 2 | 3.28 |
| 4 | 4 | 6.56 |
| 5 | 4 | 6.56 |
| 6 | 5 | 8.19 |
| 7 | 3 | 4.92 |
| 8 | 10 | 16.39 |
| 9 | 5 | 8.19 |
| 10 | 4 | 6.56 |
| 11 | 3 | 4.92 |
| 12 | 5 | 8.19 |
| 13 | 1 | 1.64 |
| 14 | 4 | 6.56 |
| 15 | 2 | 3.28 |
| 16 | 4 | 6.56 |
| 17 | 2 | 3.28 |
| 18 | 0 | 0 |
| 19 | 0 | 0 |
| 20 | 1 | 1.64 |
| ድምር | 61 | 100 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ 4.2 ማየት እንደሚቻለው የጥናቱ ተተኳሪ 61 ተማሪዎች ሲሆኑ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናው ከ20 የታረመ ነው፡፡ ከፍተኛው ውጤት 20 ከሃያ ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት ደግሞ 2 ከሃያ ነው፡፡ በዚሁ በአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት በቁጥር አንጻራዊ ብዛት ባላቸው ተማሪዎች የተመዘገበ አንድ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤቶች (Mode) አለ፡፡ ይኸውም በአንብቦ የመረዳት ውጤት (8 ከሃያ ያመጡ) ብዙ ድግግሞሽ (Mode) 10 ሲሆን ይህን ያስመዘገቡ ተማሪዎች 16.39% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

ከአጠቃላይ ተፈታኞች ውስጥ 35 (57.37%) የሚሆኑት ተጠኚዎች 9 እና ከዚያ በታች ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ 26 (42.63%) የሚሆኑት ደግሞ ከ10-20 ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ካስመዘገቡት ውጤት መረዳት የሚቻለው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተጠኚዎች አንብቦ መረዳት ችግር እንዳለባቸው ነው፡፡ ከላይ የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ እና ሁለት ላይ እንደተገለፀው 9 እና ከዚያ በታች ውጤት ያመጡ ተጠኚዎች ከ60.66% ወደ 57.37% ቢቀንስም ምንም ሰፊ ለውጥ ያሳየ ውጤት አድርጎ መውሰድ አይቻልም፡፡ ስለዚህ ከዚህ ካስመዘገቡት ውጤት መረዳት የሚቻለው ተጠኚዎቹ የአንብቦ መረዳት ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸው ነው፡፡

በአንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ሁለት በተጠኚዎች የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛው 20 ከሃያ ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት 2 ከሃያ ነው፡፡ ከአባሪ 3 ላይ ማየት እንደሚቻለው የፈተና ሁለት አማካይ አንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ውጤት 9.38 ሲሆን፣ መደበኛ ልይይት 4.255052 ነው፡፡ ሁለቱንም የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ስንመለከት የሁለቱም አማካይ ውጤት ዝቅተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም አብዛኛው ተማሪ ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ የሁለቱ ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት 9.02 ሲሆን አማካይ መደበኛ ልይይቱም 4.158292 ነው፡፡ ስለዚህ ከተገኘው ውጤት አብዛኛዎቹ ተጠኚዎች በአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡

### 4.1.3 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ

የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ መለኪያዎች በተለያዩ ምሁራን ተዘግቧል፡፡ እንደ Nation (2009:71) በጥንቃቄ የተሞላ የዝምታ ንባብ አንባቢዎች የአንብቦ መረዳት ፈተና ላይ ከአስር ሰባት ወይም ስምንት ነጥብ ማግኘት አለባቸው ይላሉ፡፡ ከአስር ስድስት ወይም ከዚያ በታች ያሉት ውጤቶች በጣም ዝቅተኛ እና አንባቢው ንባቡን እስኪረዳ ድረስ ቀጣይ ጽሑፎችን በተመሳሳይ ፍጥነት ማንበብ አለበት፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ጥሩ አንባቢ በፈተናው ከመቶ 70% እስከ 80% ማስመዝገብ ይኖርበታል፡፡ የተፈታኙ ውጤት ከ80% በላይ ከሆነ በጣም ጥሩ ችሎታ ሲኖረው ውጤቱም ደግሞ 60% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ግን ችሎታው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ነው ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ Kaval (1979፡ 27) ደግሞ በአንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ከ75% - 90% ያገኘ ተማሪ አንብቦ የመረዳት ችሎታው በቂ ሲሆን፣ ተፈታኙ 90% ወይም ከዚያ በላይ ካገኘ አንብቦ የመረዳት ችሎታው ከፍተኛ እና ውጤቱ ከ75% በታች ከሆነ ግን ዝቅተኛ ነው በማለት ያስቀምጣሉ፡፡ ይኸውም

ችሎታው በቂ ደረጃ ላይ ለመድረስ የተፈታኙ ውጤት ከ75% በላይ ማምጣት እንዳለበት ያሳያል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.3፡- የተጠኝዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ በሁለቱ ፈተናዎች**

| ከ20 % ያስመዘገቡት ውጤት | ፈተና አንድ | | ፈተና ሁለት | | አማካኝ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 1-4 | 12 | 19.67 | 8 | 13.11 | 10 | 16.39 |
| 5-8 | 21 | 34.43 | 22 | 36.07 | 21.5 | 35.25 |
| 9-12 | 12 | 19.67 | 17 | 27.87 | 14.5 | 23.77 |
| 13-16 | 12 | 19.67 | 11 | 18.03 | 11.5 | 18.85 |
| 17-20 | 4 | 6.56 | 3 | 4.92 | 3.5 | 5.74 |
| **ድምር** | 61 | 100 | 61 | 100 | 61 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ 4.3 ላይ እንደተመለከተው በአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ 45 (73.77%) ተጠኚዎች 12 እና ከዚህ በታች ከ20 ያገኙት ውጤት ሲሆን 16 (26.23%) ተጠኚዎች ግን 13 እና ከዚህ በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ናቸው፡፡ በሁለተኛው የአንብቦ መረዳት ፈተና ደግሞ 47 (77.05%) ተጠኚዎች 12 ከ20 በታች ያገኙት ውጤት ሲሆን 14 (22.95%) ተጠኚዎች ግን 13 እና ከዚያ በላይ ውጤት ያመጡ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል 12 (19.67%) ተጠኚዎች ከ65-80% ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆን 4 (6.56%) ተጠኚዎች ደግሞ ከ85% በላይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

የሁለተኛው ፈተና ውጤት ስንመለከት 47 (77.05%) ተጠኚዎች 12 እና ከዚህ በታች ከ20 ያገኙት ውጤት ሲሆን 14 (22.95%) ተጠኚዎች ግን ከ13 በላይ ውጤት ያመጡ ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር ደግሞ 11 (18.03%) ተጠኚዎች ከ65-80% ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆን 3 (4.92%) ተጠኚዎች ደግሞ ከ85% በላይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ስለዚህ ከ65-80% ውጤት ያስመዘገቡ ተጠኚዎች ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዳላቸውና 85% ውጤት ያስመዘገቡት በጣም ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አላቸው፡፡ ይህንን ሃሳብ በመደግፍ Nation (2009:71) እንደሚገልፀው ጥሩ አንባቢ በፈተናው ከመቶ 70% እስከ 80% ማስመዝገብ ይኖርበታል፡፡ የተፈታኙ ውጤት ከ80% በላይ ከሆነ በጣም ጥሩ ችሎታ

ሲኖረው ውጤቱም ደግሞ 60% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ግን ችሎታው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ነው ይላል።

የሁለቱን ፈተናዎች አማካኝ ውጤት በተመለከተ ደግሞ 46 (75.41%) ተጠኚዎች 12 እና ከዚህ በታች ከ20 ያገኙት ውጤት ሲሆን 15 (24.59%) ተጠኚዎች ግን ከ13 ከ20 በላይ ውጤት ያመጡ ናቸው። ከዚህ መረዳት የምንችለው ብዙ ተጠኚዎች በአንብቦ መረዳት ፈተናዎቹ በጣም ዝቅተኛ ውጤት እንዳስመዘገቡና በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆናቸውን ነው። ይኸውም Nation (2009:71) ውጤቱ 60% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ግን ችሎታው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ነው ከሚለው ጋር ይደጋገፋል። ነገር ግን ከተጠኚዎች መካከል 3.5 (5.74%) 17 ከ20 በላይ ያስመዘገቡና በጣም ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዳለቸው መረዳት ይቻላል። ይህ ግን ከአጠቃላዩ ተጠኚዎች አንፃር ሲታይ እጅግ አነስተኛ ነው።

## 4.2 የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድና ሁለት ዝርዝር መረጃዎች

የዚህ ጥናት አንዱ ትኩረት የሆነው በሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የ10ኛ ክፍል በኦሮምኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ፍጥነት ላይ ነው። በዚህ መሰረት የተጠኚዎቹ የንባብ ፍጥነት ያለበትን ደረጃ በጥናት አፈላልጎ ማግኘት ነው፡፡ ስለዚህ ተጠኚዎች የተፈተኑትን የንባብ ፈተናዎች በደቂቃ ምን ያህል ቃላትን ማንበብ እንደቻሉ ከዚህ በታች በሚቀርቡት ሠንጠረገዦች ቀርቧል፡፡ አባሪ “4”ን ይመልከቱ፡፡

### 4.2.1 የፈተና አንድ የተጠኚ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት

የተጠኚዎችን የንባብ ፍጥነትን ለመስራት Nuttal (1982፡36) የንባብ ፍጥነት መለኪያ ቀመር ጥቅም ላይ ውሏል። የንባብ ፍጥነት ማለት አንድ አንባቢ ከተሰጠው ምንባብ ላይ በደቂቃ ምን ያህል ቃላትን እንደሚያነብ የሚያሳይ ሲሆን የንባብ ፍጥነት የሚለካው በደቂቃ ውስጥ በተነበበው የቃላት ብዛት ይሆናል።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው አንድ አንባቢ የተሰጠውን ምንባብ አንብቦ ለመጨረስ የፈጀበትን ሴኮንዶች በመውሰድ በደቂቃ ምን ያህል ቃላትን እንዳነበበ ለማወቅ የሚረዳ ነው። ስለዚህ ከዚህ በታች በተቀመጠው ቀመር መሰረት የእያንዳንዱ ተጠኚ አንብቦ የጨረሰበት ጊዜ ተሰልቶ በሰንጠረዥ 4.4 እና 4.5 ለሁለቱም ፈተናዎች ተሰልቶ ተቀምጧል።

X/yx6 = Z

X = በጽሁፍ ውስጥ ያሉት የቃላት ብዛት

Y = በጽሁፍ ውስጥ ያሉት ቃላት ለማንበብ የወሰደው ሰዓት በየአስር ሴኮንድ ልዩነት

6 = በደቂቃ ውስጥ የሚኖር የ10 ሴኮንድ ልዩነት

Z = በደቂቃ ውስጥ የሚነበበውን የቃላት ብዛት የሚያመላክት ነው

ለምሳሌ የፈጣን አንባቢ ፍጥነት ውጤትን እንመልከት

316/13.6x6= Z

በደቂቃ 139 ቃላትን አንብቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.4፡- የፈተና አንድ የንባብ ፍጥነት ውጤት**

| የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት የቃላት ብዛት በደቂቃ በፈተና አንድ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 31 | 1 | 1.64 |
| 32 | 2 | 3.28 |
| 34 | 6 | 9.83 |
| 35 | 2 | 3.28 |
| 39 | 1 | 1.64 |
| 43 | 1 | 1.64 |
| 44 | 3 | 4.92 |
| 45 | 3 | 4.92 |
| 47 | 1 | 1.64 |
| 48 | 4 | 6.56 |
| 50 | 1 | 1.64 |
| 51 | 2 | 3.28 |

| | | |
|---|---|---|
| 53 | 3 | 4.92 |
| 56 | 3 | 4.92 |
| 58 | 2 | 3.28 |
| 59 | 1 | 1.64 |
| 60 | 4 | 6.56 |
| 61 | 1 | 1.64 |
| 62 | 1 | 1.64 |
| 63 | 2 | 3.28 |
| 64 | 2 | 3.28 |
| 65 | 1 | 1.64 |
| 67 | 1 | 1.64 |
| 73 | 1 | 1.64 |
| 74 | 1 | 1.64 |
| 75 | 2 | 3.28 |
| 77 | 1 | 1.64 |
| 79 | 2 | 3.28 |
| 81 | 1 | 1.64 |
| 84 | 1 | 1.64 |
| 97 | 1 | 1.64 |
| 104 | 1 | 1.64 |
| 110 | 1 | 1.64 |
| 139 | 1 | 1.64 |
| ድምር | 61 | 100 |

ከሠንጠረዥ 4.4 ላይ ማየት እንደሚቻለው በፈተና አንድ የንባብ ፍጥነት ከ61 ተጠኚዎች መካከል አንድ ተጠኚ በደቂቃ 139 ቃላትን ማንበብ የቻለ ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ ውጤት አንፃር ሲታይ 1.64% ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከ61 ተጠኚዎች መካከል ዝቅተኛው የንባብ ፍጥነት ወይም ዝግተኛ አንባቢዎች 1 ተጠኚ (1.64%) 31 ቃላት በደቂቃ ያነበቡ ወይም ያስመዘገቡት ውጤት ነው፡፡

ከ61 ተጠኚዎች መካከል 57 ተማሪዎች በደቂቃ ከ97 ቃላት በታች አንብበዋል፡፡ 4 ተማሪዎች ደግሞ ከ97-139 ቃላትን በደቂቃ የንባብ ፍጥነትን አስመዝግበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት በጣም የተበታተነ ሲሆን በፈጣን አንባቢና በአዝጋሚ አንባቢ መካከል ያለው ልዩነት 108 ቃላት በደቂቃ ነው፡፡ በአጠቃላይ የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት ከክፍል ደረጃቸው አንፃር በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ የፈተና አንድ አማካይ የንባብ ፍጥነት በደቂቃ 52 ቃላት ሲሆን ከዚህ መረዳት የሚቻለው አብዛኛው የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች እጅግ በጣም ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት እንዳስመዘገቡ ነው፡፡

### 4.2.2 የፈተና ሁለት የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት

**ሠንጠረዥ 4.5፡- የፈተና ሁለት የንባብ ፍጥነት ውጤት**

| የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት የቃላት ብዛት በደቂቃ በፈተና ሁለት | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 33 | 1 | 1.64 |
| 34 | 1 | 1.64 |
| 35 | 3 | 4.92 |
| 36 | 4 | 6.56 |
| 37 | 2 | 3.28 |
| 38 | 1 | 1.64 |
| 39 | 2 | 3.28 |
| 41 | 1 | 1.64 |

| | | |
|---|---|---|
| 43 | 4 | 6.56 |
| 45 | 1 | 1.64 |
| 47 | 2 | 3.28 |
| 48 | 3 | 4.92 |
| 49 | 2 | 3.28 |
| 51 | 3 | 4.92 |
| 53 | 6 | 9.83 |
| 56 | 1 | 1.64 |
| 57 | 3 | 4.92 |
| 58 | 2 | 3.28 |
| 59 | 3 | 4.92 |
| 60 | 1 | 1.64 |
| 61 | 1 | 1.64 |
| 65 | 2 | 3.28 |
| 66 | 1 | 1.64 |
| 68 | 1 | 1.64 |
| 69 | 2 | 3.28 |
| 74 | 2 | 3.28 |
| 92 | 1 | 1.64 |
| 93 | 2 | 3.28 |
| 95 | 1 | 1.64 |
| 96 | 1 | 1.64 |
| 136 | 1 | 1.64 |
| **ድምር** | 61 | 100 |

በሠንጠረዥ 4.5 ላይ እንደተቀመጠው 61 ተጠኚዎች የንባብ ፍጥነታቸው ከ33 እስከ 136 ቃላት በደቂቃ ሲሆን ልዩነቱም 103 ቃላት በደቂቃ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁለተኛው ምንባብ 1 (1.64%) ፈጣን አንባቢ ለመጨረስ የወሰደበት ጊዜ 172 ሴኮንድ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ 1 (1.64%) ዝግተኛ አንባቢ ምንባቡን ለመጨረስ 720 ሴኮንድ ወስዶባቸዋል፡፡ ከዚህ

መረዳት የሚቻለው በፈጣን እና ዝግተኛው አንባቢ መካከል ያለው የንባብ ፍጥነት እጅግ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ነው።

የዚህ ንባብ ፍጥነት ውጤት እንደሚያመለክተው ከ61 ተጠኚዎች መካከል 58 ተማሪዎች በደቂቃ ከ95 ቃላት በታች አንብበዋል። 3 ተማሪዎች ደግሞ ከ95-136 ቃላትን በደቂቃ የንባብ ፍጥነትን አስመዝግበዋል። ከዚህ በተጨማሪ የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት በጣም የተበታተነ ነው። በአጠቃላይ የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት ከክፍል ደረጃቸው አንፃር እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው። የንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት አማካይ የንባብ ፍጥነት በደቂቃ 50.2 ቃላት ሲሆን ከዚህ መረዳት የሚቻለው አብዛኛው የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች እጅግ በጣም ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት እንዳስመዘገቡ ነው። ነገር ግን ይህ ውጤት ወደ ፊት ሊሻሻል የሚችል ሊሆን ይችላል። የዚህ ፈተና የተጠኚዎች አማካይ የንባብ ፍጥነት ከመጀመሪያው ፈተና 52 ቃላት በደቂቃ ጋር ሲወዳደር ትንሽ ዝቅ ብሏል። ምክንያቱም የቃላት ብዛቱ ከፍ ስለሚል ጭምር ነው።

የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድና ሁለትን የእያንዳንዱ የተጠኙዎች ንባብ ፍጥነት እና መደበኛ ልይይቱም ከአባሪ አራት ላይ ማየት ይቻላል።

### 4.2.3 የፈተና አንድና ሁለት አማካይ የቃላት ብዛትና የማንበብ ፍጥነት

**ሠንጠረዥ 4.6፡- የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች አማካይ የንባብ ፍጥነት የሚያሳይ መረጃ**

| የተጠኚዎች አማካይ የንባብ ፍጥነት ቃላት ብዛት በደቂቃ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 33 | 2 | 3.28 |
| 34 | 3 | 4.92 |
| 35 | 2 | 3.28 |
| 36 | 3 | 4.92 |
| 37 | 1 | 1.64 |
| 38 | 1 | 1.64 |
| 39 | 1 | 1.64 |
| 41 | 1 | 1.64 |
| 43 | 1 | 1.64 |
| 44 | 2 | 3.28 |

| | | |
|---|---|---|
| 45 | 1 | 1.64 |
| 46 | 2 | 3.28 |
| 47 | 1 | 1.64 |
| 48 | 3 | 4.92 |
| 49 | 1 | 1.64 |
| 50 | 1 | 1.64 |
| 51 | 3 | 4.92 |
| 53 | 2 | 3.28 |
| 54 | 2 | 3.28 |
| 55 | 1 | 1.64 |
| 57 | 2 | 3.28 |
| 58 | 1 | 1.64 |
| 59 | 3 | 4.92 |
| 61 | 2 | 3.28 |
| 62 | 4 | 6.56 |
| 64 | 1 | 1.64 |
| 65 | 1 | 1.64 |
| 66 | 3 | 4.92 |
| 70 | 1 | 1.64 |
| 72 | 1 | 1.64 |
| 73 | 1 | 1.64 |
| 74 | 1 | 1.64 |
| 86 | 1 | 1.64 |
| 87 | 1 | 1.64 |
| 89 | 1 | 1.64 |
| 96 | 1 | 1.64 |
| 102 | 1 | 1.64 |
| 138 | 1 | 1.64 |
| **ድምር** | 61 | 100 |

ሠንጠረዥ 4.6 ላይ የሁለቱ ፈተናዎች የንባብ ፍጥነት አማካይ ተቀምጧል፡፡ ይኸውም ከዝቅተኛው አንባቢ እስከ ከፍተኛው ፈጣን አንባቢ ድረስ በቅደም ተከተል ከድግግሞሹ እና መቶኛ ጋር ተሰልቷል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ተጠኚ ምን ያህል ቃላት በደቂቃ በአማካይ እንዳነበበ ቀደም ሲል በተገለፀው የNuttal (1982፡36) የንባብ ፍጥነት መለኪያ ማሳያ ቀመርን በመጠቀም ስሌቱ ተቀምጧል፡፡ ከፍተኛ ድግግሞሹ (mode) 4 ሲሆን የተመዘገበውም በ4 (6.56%) ተጠኚዎች ነው፡፡

የምንባቦቹ አማካይ የቃላት ብዛት 354

ምንባቦቹን አንብቦ ለመጨረስ የፈጀው አማካይ ሰከንዶች 417.14 (አባሪ አራትን ይመልከቱ)

X/yx6 = Z

X = በጽሁፍ ውስጥ ያሉት የቃላት ብዛት

Y = በጽሁፍ ውስጥ ያሉት ቃላት ለማንበብ የወሰደው ሰዓት በየአስር

ሴኮንድ ልዩነት

6 = በደቂቃ ውስጥ የሚኖር የ10 ሴኮንድ ልዩነት

Z = በደቂቃ ውስጥ የሚነበበውን የቃላት ብዛት የሚያመላክት ነው

**Z =354/41.714 x6**

**Z =50.92**

ከላይ በተቀመጠው ስሌት መሰረት የንባብ ፍጥነት አማካይ ውጤት ደግሞ 50.92 ነው። ይህም ተጠኚዎች በአማካይ 51 ቃላትን በደቂቃ አንብበዋል ማለት ነው። ነገር ግን አማካይ ዝቅተኛ አንባቢ 33 ቃላትን በደቂቃ ያነበቡ ሲሆን ፈጣን አንባቢ ደግሞ 138 ቃላትን በደቂቃ አንብበዋል። ከ61 ተጠኚዎች መካከል 3 (4.92%) ከ138-96 ቃላትን በደቂቃ ያነበቡ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ 58 (95.08%) የሚሆኑት ተጠኚዎች ደግሞ ከ89-33 ቃላትን በደቂቃ አንብበዋል። ስለዚህ በጥናቱ መሰረት አብዛኛው ተጠኚ የፍጥነት ንባብ ችግር እንዳለበት መረዳት ይቻላል።

## 4.3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ጋር ያለው ግንኙነት

ይህ ጥናት ዓላማው በኦሮምኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን እና የንባብ ፍጥነታቸውን ማጥናት ነው። ስለዚህ ለዚህ ጥናት ሲባል የ61 ተጠኚ ተማሪዎች የአንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አንፃር ፍተሻ ተደርጓል። ውጤቱም እንደሚከተለው ቀርቧል።

**ሠንጠረዥ 4.7፡- አማካይ የተጠኚዎች አንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት**

| በደቂቃ ያነበቡት የቃላት ብዛት በአማካይ | በደቂቃ ከአማካይ በታች ያነበቡ ተጠኚዎች ብዛት | በደቂቃ ከአማካይ በላይ ያነበቡ ተጠኚዎች ብዛት | አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና በአማካይ ውጤት ከ20% |
|---|---|---|---|
| 51 | 26 (42.62%) | 35(57.38%) | 9.02 |

ከሠንጠረዥ 4.7 መመልከት እንደሚቻለው በኦሮምኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የንባብ ፍጥነታቸው በአማካይ 51 ቃላት በደቂቃ ሲሆን ከአማካዩ በታች ያነበቡ ተማሪዎች ደግሞ 26 (42.62%) ሲሆኑ ከአማካዩ በላይ ያነበቡ ተማሪዎች ደግሞ 35 (57.38%) ናቸው፡፡ ይኸውም ብዙ ተጠኚዎች ከአማካይ በታች መሆናቸውንና በጣም ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤታቸውን ከ20% ስንመለከት ደግሞ 9.02 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ስለዚህ የንባብ ፍጥነታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆናቸውን ያሳየ ነው፡፡

## 4.4. የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ግንኙነት በፈተና አንድ

ከአባሪ 4 ላይ እንደተመለከተው በንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ ፈጣን አንባቢ 316 ቃላትን በ136 ሴኮንድ ያነበበ ሲሆን ዝግተኛ አንብቢዎች ደግሞ በ603 ሴኮንድ አንብበዋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና አንድ ውጤትን ስንመለከት ከፍተኛው 18 ከ20 ሲሆን ዝቅተኛው 2 ከ20 ነው፡፡ 18 ከ20 ውጤት የተመዘገበው በፈጣን አንባቢ ሲሆን 2 እና 3 ከሃያ የተመዘገበው በዝግተኛ አንባቢዎች ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ የምንረዳው በፍጥነት አንብበው የጨረሱ አንባቢዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው የተሻለና ውጤታው በጣም ጥሩ እንደሆነ ነው፡፡ ይኸውም ለማንበብ የፈጀው ሰዓት ሲቀንስ አንብቦ የመረዳት ችሎታና ውጤት ይጨምራል ማለት ነው፡፡

## 4.5 የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ግንኙነት በፈተና ሁለት

በንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት ፈጣን አንባቢዎች 391 ቃላትን በ172 ሴኮንድ ያነበቡ ሲሆን ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ በ720 ሴኮንድ አንብበዋል። የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ሁለት ውጤትን ስንመለከት ከፍተኛው 20 ከ20 ሲሆን ዝቅተኛው 2 ከ20 ነው። 20 ከ20 ውጤት የተመዘገበው በመካከለኛ አንባቢ ሲሆን ፈጣን አንባቢው 16 ከ20 አግኝቷል። 2 እና 3 ከሃያ የተመዘገበው በዝግተኛ አንባቢዎች ነው። ስለዚህ ከዚህ የምንረዳው በፍጥነት አንብበው የጨረሱ አንባቢዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው የተሻለና ውጤታው በጣም ጥሩ እንደሆነ ነው። ይኸውም ለማንበብ የፈጀው ሰዓት ሲቀንስ አንብቦ የመረዳት ችሎታና ውጤት ጨምሯል ማለት ነው። ስለዚህ የንባብ ፍጥነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤቶች አንዱ ሲጨምር ሌላው ይቀንሳል ማለት ነው።

## 4.6 የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የማንበብ ፍጥነት ተዛምዶ

በአንብቦ መረዳት እና በንባብ ፍጥነት መካከል ያለው ተዛምዶ ለመለየት በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት ኮሬሌሽን (Pearson product moment correlation) የስሌት ቀመርን በመጠቀም በባለሙያ ድጋፍ ተሰርቶ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ላይ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.8፡- የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ልኬት በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት ኮሬሌሽን**

| የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች | | የንባብ ፍጥነት መለኪያ ፈተና 1 | የንባብ ፍጥነት መለኪያ ፈተና 2 | አማካይ |
|---|---|---|---|---|
| አንብቦ የመረዳት ፈተና 1 | የፒርሰን ተዛምዶ | -0.2893727 * | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አንብቦ የመረዳት ፈተና 2 | የፒርሰን ተዛምዶ | | -0.4112915*** | |
| አማካይ | የፒርሰን ተዛምዶ | | | -0.371252** |

በሠንጠረዥ 4.8 ላይ የቀረበው የፒርሰን ተዛምዶ ልኬት ውጤቱ እንደሚያመለክተው በተጠኚዎቹ የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አንድ እና የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ መካከል በባለ ሁለት ጫፍ ትይዩ አሉታዊ ተዛምዶው (-0.2893727*) እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡ ይህም ማለት የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነታቸውም ጊዜ ሲጨምር የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መቀነስ ማሳየቱን ነው፡፡ ይኸውም ያለው (2011፣328) ስለ አሉታዊ ተዛምዶ ሲገልፁ ሁለት ተዛማጅ ተለዋዋጮች በተመሳሳይ አቅጣጫ አብረው ከመቀነስ ወይም ከመጨመር ይልቅ አንደኛው ሲጨምር ሌላኛው ሲቀንስ የሚስተዋል ግንኙነት ነው ይላሉ፡፡ የዚህ ጥናት ውጤትም ከዚህ ጋር ይገናኛል፡፡ የኮከብ ምልክቷ የምታሳየው ተዛምዶ መኖሩን ነው፡፡ ይኸውም የፈጣን አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከፍተኛ ሲሆን ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ከተጠቀሰው ስሌት መረዳት የሚቻለው አሉታዊ የፒርሰን ተዛምዶ ቁጥሩ የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነታቸው ዝቅ እያለ (ከፍ ያለ ጊዜ ሲወስድ) ሲሄድ የአንብቦ መረዳታቸው ውጤት አነስተኛ መሆኑን ነው፡፡

ሁለተኛው የአንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች መካከል ደግሞ ጠንካራ የሆነ መጠን በባለ ሁለት ጫፍ ትይዩ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ (-0.4112915***) እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡ ይህም ማለት የተጠኚዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤታቸው ዝቅተኛ ሲሆን አንብበው የጨረሱበት ጊዜ ከፍ ያለ መሆኑን ማሳየቱን ነው፡፡ የኮከብ ምልክቶቹ ከፍተኛ ተዛምዶ መኖሩን ነው፡፡ የፒርሰን ተዛምዶው ከ1.00 ያለው ርቀት (-0.4112915***) ጠንካራ ሲሆን አቅጣጫው አሉታዊ ነው፡፡ እንደ ያለው (2011፣328) በሁለት ተለዋዋጮች መካከል የሚገኝ ተዛምዶ መጠን ከ +1 እስከ -1 ድረስ ነው፡፡ ውጤቱ ከ 0 ወደ +1 እየቀረበ ሲመጣ የተዛምዶ መጠን ጠንካራ ሲሆን አቅጣጫው

አዎንታዊ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ውጤቱ ከ 0 ወደ -1 ሲቀርብ ተዛምዶው ጠንካራ አቅጣጫው ደግሞ አሉታዊ ነው። ስለዚህ የዚህ ጥናት ውጤት -0.4112915 ጠንካራ ተዛምዶና አሉታዊ አቅጣጫ ያሳያል።

የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች አማካይ እና የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች አማካይ መካከልም ጠንካራ የሆነ መጠን በባለ ሁለት ጫፍ ትይዩ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ (-0.371252**) ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በአማካይ የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነታቸውም ጊዜ ከፍ ሲል የአንብቦ መረዳት ችሎታ የቀነሰ ይሆናል። የኮኮብ ምልክቶቹ ጠንካራ ተዛምዶ መኖሩን ነው። የፒርሰን ተዛምዶው ከ1.00 ያለው ርቀት (-0.371252**) ጉልህ ነው። በአጠቃላይ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተጠኚ ተማሪዎች የአንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት መካከል ባለ ሁለት ጫፍ ጉልህ አሉታዊ ተዛምዶ መኖሩን ከጥናት ውጤቱ ማየት ይቻላል።

## 4.7. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነትን ተዛምዶ መፈተሽ ነው። የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ተዛምዷዊ የምርምር ስልት ጥቅም ላይ ውሏል። በተጨማሪም የአጠናን ዘዴው መጠናዊ የምርምር ዘዴን እና ዓይነታዊ የምርምር ስልትን (ቅይጥ ዘዴ) ነው። ለጥናቱ መሰብሰቢያነት የሚዉሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ፈተና እና የማንበብ ፍጥነት መለኪያ ፈተናዎች ናቸው። ስለሆነም በፈተናዎቹ ላይ በመመርኮዝ የተጠኚ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት በሠንጠረዥ 4.1. እና 4.2. ተተንትኖ ቀርቧል። ከሠንጠረዥ 4.3 መመልከት እንደሚቻለው በሁለቱ ፈተናዎች የተጠኚ ተማሪዎቹ የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች አማካይ ውጤት 9.02 ሲሆን አማካይ መደበኛ ልይይቱም 4.154983 ነው። ስለዚህ ከተገኘው ውጤት አብዛኛዎቹ ተጠኚዎች በአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በተጨማሪም የተጠኚዎችን የንባብ ፍጥነትን ለመስራት Nuttal (1982:36) የንባብ ፍጥነት መለኪያ ቀመር ጥቅም ላይ ውሏል። ይኸውም የንባብ ፍጥነት የሚለካው በደቂቃ ውስጥ በተነበበው የቃላት ብዛት ይሆናል። የሁለቱ የንባብ ፍጥነት አማካይ በሠንጠረዥ 4.6 ላይ

ተቀምጧል። ይኸውም ከዝቅተኛው አንባቢ እስከ ከፍተኛው ፈጣን አንባቢ ድረስ በቅደም ተከተል ከድግግሞሹ እና መቶኛ ጋር ተሰልቷል። ከፍተኛ ድግግሞሹ (mode) 4 ሲሆን የተመዘገበውም በ4 (6.56%) ተጠኚዎች ነው። የንባብ ፍጥነት አማካይ ውጤት ደግሞ 50.92 ነው። ይህም ተጠኚዎች በአማካይ 51 ቃላትን በደቂቃ አንብበዋል ማለት ነው። ነገር ግን አማካይ ዝቅተኛ አንባቢ 33 ቃላትን በደቂቃ ያነበቡ ሲሆን ፈጣን አንባቢ ደግሞ 138 ቃላትን በደቂቃ አንብበዋል። ስለዚህ በጥናቱ መሰረት አብዛኛው ተጠኚ የፍጥነት ንባብ ችግር እንዳለበት መረዳት ይቻላል።

በሌላ በኩል የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶን ለመለካት የተገኙት ውጤቶች በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት ኮረሌሽን (Pearson product moment correlation) ስሌት ቀመር አማካኝነት ትንተና ተደርጎባቸዋል። ከሠንጠረዥ 4.8. ላይ እንደተመለከተው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች አማካይ እና የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች አማካይ -0.371252 ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም የሚያሳየው ዝቅተኛ የሆነ ባለ ሁለት ጫፍ ትይዩ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በአማካይ የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነታቸው ጊዜ ከፍ ሲል የአንብቦ መረዳት ችሎታ የቀነሰ ይሆናል። የፒርሰን ተዛምዶው ርቀት በባለ ሁለት ጫፍ ትይዩ ከ +1 እስከ -1 ያለው ርቀት ላይ መታየት አለበት። በዘህ ጥናት ግኝት መሰረት አማካዩ -0.371252 ነው። በአጠቃላይ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተጠኚ ተማሪዎች የአንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት መካከል ባለ ሁለት ጫፍ ዝቅተኛ አሉታዊ ተዛምዶ መኖሩን የጥናቱ ውጤቱ አሳይቷል።

በዚህ ጥናት መሰረት የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ፍተሻ እንዳመለከተው ተጠኚዎች ዝቅተኛ የሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት እንዳላቸው ሲሆን ተዛምዶውም ጠንካራ አሉታዊ ተዛምዶ መሆኑን ነው። የዚህ ጥናት ውጤት ከቀደምት ጥናቶች ከWijaya (2018:83)፣ ተስፋዬ (2001)፣ አያሌው (2001) በረከት (2010)፣ ዮሐንስ (2013) እና ታሪኳ የማታ (2015) ጋር ተቀራራቢነት አለው። ይኸውም በአጠቃላይ የኢአፈ ፈት ቋንቋ ተጠኚ ተማሪዎች የአንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው።

በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ከዚህ ጥናት መረዳት የሚቻለው በንባብ ፍጥነት ፈተና ከፍ ያለ ጊዜ የወሰደባቸው ተጠኚዎች የአንብቦ መረዳት ውጤታቸው

ዝቅ ያለ እንደሆነና በተቃራኒው  በንባብ ፍጥነት ፈተና ዝቅተኛ ጊዜ የወሰደባቸው ተጠኚዎች የአንብቦ መረዳት ውጤታቸው ከፍ ያለ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ መረዳት ጋር በአሉታዊም ይሁን በአዎንታዊ መልኩ ተዛምዶ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ጥናቱ ከፍ ያለ አሉታዊ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡

## ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያና አስተያየት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሞሌ መንደራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል በኦሮምኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች የአንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት መካከል ያለውን ተዛምዶን መፈተሽ ነው። የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው። እነሱም አንደኛ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ይገኛል? ሁለተኛ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ፍጥነታቸው ምን ይመስላል? እና ሶስተኛ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነትጋር ያለው ግንኙነት ምን ያህል ነው? የሚሉ ናቸው። እነዚህን ሦስቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ የተጠኚዎቹን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት በሁለት ፈተናዎች በተናጠል ከመረመረ በኋላ በተጠኚዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት መካከል ያለውን ተዛምዶ ፍተሻ አድርጓል። ይኸውም የጥናቱ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ በምእራፍ አራት በቀረበው መሰረት ከዚህ በታች የቀረበው ማጠቃለያ ተሰጥቷል።

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ምእራፍ አንድ ላይ ዐቢይና ዝርዝር ዓላማዎች ሲኖሩት ጥናቱን ለመፈፀም ሶስት መሪ ጥያቄዎችን አንግቦ የተነሳ ነው። በምእራፍ ሁለት ስር ደግሞ ስለ ንባብ ምንነት፣ አንብቦ መረዳት እና የንባብ ፍጥነት ምንነት፣ የአንብቦ መረዳት እና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶን በሚመለከት በምሁራን የተሰነዘሩ ሃሳቦችና አስተያየቶች ቅኝት ተደርጎባቸዋል። በምእራፍ ሶስት ደግሞ ለዚህ ጥናት መሳካት የሚረዱ የጥናት ዘዴዎች፣ የጥናቱ ተሳታፊዎች የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ እና የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ዘዴ ተካቶበታል። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ለተጠኚዎች በተሰጡ ፈተናዎች አማካኝነት ነው። በምእራፍ አራት ስር ደግሞ የተገኙት መረጃዎች ሰፊ ትንታኔዎች ተሰጥቶባቸዋል።

የጥናቱ ግኝት እንዳመለከተው ተጠኚዎቹ በሁለቱ የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች አማካይ ውጤታቸው 9.02 ሲሆን ከተገኘው ውጤት አብዛኛዎቹ ተጠኚዎች በአንብቦ መረዳት

ችሎታ ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ስለዚህ የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ብቃት ላይ ችግር እንዳለ አመላካች ነው።

በጥናቱ ግኝት መሰረት ከተጠኚዎች መካከል 39 (63.93%) የሚሆኑት ከተሰጣቸው ፈተናዎች በአማካዩ ከአጋማሹ 10 ከ20 በታች ያገኙ ናቸው፣ ነገር ግን ከማለፊያ ነጥቡ 10 እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች 22 (36.07%) ሲሆኑ ከፍተኛው አማካይ ነጥብ 18 ከ20 ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም የሚያሳየው ብዙ ተጠኚ ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ፈተናው ማለፊያ ማርክ ማግኘት አለመቻላቸውን ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ወደ 64% የሚጠጉት ተጠኚዎች በኢአፍ-ፈት ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን አመላካች ነው።

አማካይ የንባብ ፍጥነት ውጤትን ስንመለከት ደግሞ ከተጠኚዎች መካከል 3 (4.92%) ከ96-138 ቃላትን በደቂቃ ያነበቡ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ 58 (95.08%) የሚሆኑት ተጠኚዎች ደግሞ ከ89-33 ቃላትን በደቂቃ አንብበዋል። በተጨማሪም የተጠኚ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነታቸው በአማካይ 51 ቃላት በደቂቃ ሲሆን ከአማካዩ በታች ያነበቡ ተማሪዎች ደግሞ 26 (42.62%) ናቸው። ይኸውም ብዙ ተጠኚዎች ከአማካይ በታች መሆናቸውና ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። ስለዚህ በጥናቱ መሰረት አብዛኛው የኢአፍ- ፈት ቋንቋ ተጠኚ ተማሪ ከፍ ያለ የንባብ ፍጥነት ችግር መኖሩን ጠቋሚ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በተጠኚዎቹ አማካይ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች እና የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች አማካይ መካከልም ከፍተኛ የሆነ መጠን በባለ ሁለት ጫፍ ትይዩ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ (-0.371252**) መሆኑን ከስታስቲካዊ መረጃው መመልከት ይቻላል። ይኸውም የተጠኚዎቹ የንባብ ፍጥነት ጊዜ ሲጨምር በዚያው ልክ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውም መቀነስ እንደሚያሳይ ተረጋግጧል። ስለዚህ የኢአፍ-ፈት ቋንቋ ተጠኚ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት እና የማንበብ ብቃት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት ለአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ውጤት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆን እንደ ችግር ሊቆጠር የሚችል ነው። በአጠቃላይ ተጠኚዎቹ በሁለቱም የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተናዎች አማካይ ውጤት በጣም ዝቅተኛ (9.02) መሆኑ በተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ብቃት ችግር እንዳለ አመላካች ነው።

## 5.2 አስተያየት

ይህ ጥናት የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ያላቸውን ተዛምዶ አሰሳ አድርጓል፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረት ፈጣን አንባቢዎች ከፍ ያለ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሲኖራቸው በተቃራኒው ደግሞ ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ ዝቅ ያለ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አላቸው፡፡ ስለዚህ የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ እና በክለሳ ድርሳናት በመታገዝ አጥኚዋ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሃሳቦች በመጠቆም ጥናቷን ታጠቃልላለች፡፡

- እንደ Yaman, I. & Cakici, D. (2013: 373-74) እና Oakhill, Cain, and Elbro (2015:1) የአንብቦ መረዳት ችሎታ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡ አንብቦ መረዳት ብዙ የተለያዩ የግንዛቤ ክህሎቶችን እና ችሎታዎችን ማስተባበር የሚፈልግ ውስብስብ ተግባር ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ አንብቦ መረዳት ከንባብ ፍጥነት ጋር የተዛመዱ እንደሆኑ Fry (2011፡15) እና Nuttall (1982፡33) እንዲህ በማለት ገልፀዋል፡፡ በአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት መካከል ያለው ተዛምዶ በጣም አስፈላጊ ሲሆን የንባብ ፍጥነት እና አንብቦ መረዳት በቅርበት የተሳሰሩ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ የተማሪዎች ንባብ ፍጥነታቸው ከአንብቦ ከመረዳት ጋር አዎንታዊ ግኙነት ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ዙሪያ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገቢውን ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡

- ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ንባብን በማስተማር ረገድ የበለጠ እንዲያውቁ ሊረዳቸው ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ መምህራኑ የእያንዳንዱ ተማሪ የንባብ ደረጃ እና የመረዳት ችሎታቸው የተለያዩ እንደሆኑ አድርገው ይቆጥሩ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የማንበብ ፍጥነታቸውን ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር እንዲያሻሽሉ ስልጠና ሊሰጧቸው ይገባል፡፡

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የተማሪዎችን የንባብ ክህሎት በተማሪ የንባብ ደረጃ መጠን እንዲያስተካክሉ እና የተማሪዎችን የንባብ አፈፃፀም ለማሳደግ እና ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ ተገቢ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎች የማንበብ ክህሎታቸው እየተሻሻለ ሲሄድ የአንብቦ መረዳታቸውም ይሻሻላል፡፡ ይኸውም መምህራኑ የተማሪዎቻቸውን የንባብ ፍጥነትና

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት በትብብር መማር ዘዴ የአተገባበር መርሆዎች በመከተል ቢያስተምሩ ጥሩ ነው።

- ተማሪዎች የንባብ ደረጃቸውን ምን ላይ እንዳለ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ተማሪዎቹ አንብቦ መረዳት ችሎታቸው ከንባብ ፍጥነት ጋር ለማስማማት የበለጠ ስልጠና ማግኘት አለባቸው።

- አጥኚዋ የተማሪዎች የንባብ ፍጥነት እና የአንብቦ መረዳት ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ተብለው የተመደቡ ተማሪዎችን ውጫዊ እና ውስጣዊ ሁኔታዎች እንዲመረምር ከቀጣዩ ተመራማሪ ይጠበቃል ትላለች። ከዚህም በላይ ጥናቶች ሌሎች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ለወደፊት ምርምር በማድረግ ሰፊ ተሳታፊ በመምረጥ ሊያካሄዱ ይገባል።

- ተማሪዎች የማንበብን ዓላማና እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች በተቻለ መጠን ፍጥነት ባለው ሁኔታ ጽሑፍ ለማንበብ መሞከር አለባቸው። ይኸውም በፍጥነት አንብበው የመረዳት ችሎታቸውን ሊያጎለብቱ ይገባል።

## ዋቢዎች

ማረው ዓለሙ፡፡ (2003)፡፡ ዘመናዊ *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፣* ሁለተኛ እትም፡፡አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

በረከት ሁሴን:: (2010):: "በሰገን አከባቢ ሕዝቦች በሰገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በአማርኛ ቋንቋ ኢ. አፍ ፈት የሆኑ የ9 ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ::" ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ *በስነ ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር*፡ አዲስ አበባ ፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ተስፋዬ ሽዋየ፡፡ (1986)፡፡ *አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ችሎታን ማዳበር*፡ አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድርጅት፡፡

ተሾመ ፎርሲዶ፡፡ (1997) ፡፡ "በከምባታ ጠምባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታቸውና የማንበብ ፍጥነታቸው፡፡" ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

ታሪኳ የማታ፡፡ (2015)፡፡ "በአፋን ኦሮሞ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡"ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ ጅማ (ያልታተመ)፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ (2007)፡፡ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመምህራን ማሰልጠኛ ማንዋል፡፡ አዲስ አበባ ትምህርት ሚስቴር፡፡

አለም እሸቱ (1995)፡፡ "በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር፡፡" ከጥቅምት 25 እስከ 29/1995 ዓ.ም ለአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ የ2ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች መርሃ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደ ጥናት የቀረበ ከስ/ት/ዝ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት፣ አዲስ አበባ፡፡

አያሌው አንተነህ፡፡ (2001)፡፡ "በአማርኛ ቋንቋ የፍጥነት ንባብ ክሂል ከአንባቦ የመረዳት ክሂል ጋር ያለው ተዛምዶ በወልዲያ የከፍተኛ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተመሠረተ ጥናት" ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2011)፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አቀነባበር፣ሦስተኛ እትም፡፡ ባህር ዳር፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዮሐንስ ሰለሞን (2013) ፡፡ "በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፊት የሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ትንተና በጉጂ ዞን በነገሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት፡፡" ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ ጅማ (ያልታተመ)፡፡

Afiyah, F.A. (2021). "The Correlation Student Reading Speed and Reading Comprehension Achievement of Tenth-Grade Students in Indonesia." *Jurnal Varidika*, 33(2), 165-174.

Alderson, J.C (2000). *Assessing Reading*. Cambridge: Cambridge University Press.

Arshad, A, Shakir, A. and Ahmad, M. (2020). "A Review on the Principles of a Reading Comprehension : Test Construction to Assess the Test Takers at Different Levels." *HamdardIslamicus*, 43(1), 249-263.

Bell, Timothy. (2001). "Extensive Reading: Speed and Comprehension." *The Reading Matrix*, 1(1),2.

Carrell, P.L. (2006). Can Reading Strategies be Succefully Taught? The Language Teacher Journal. JALT.

David, A. (2005). *Reading Skills in English*. Delhi: Common Wealth Publishers.

Dymoc, S. (2005). "Comprehension Strategy Instruction: Teaching Narrative Text Structure Awareness" *The Reading Teacher*, vol. 61 No.2.

Elleman Amy M. and Oslund Eric L. " Reading Comprehension Research: Implications for Practice and Policy." *Policy Insights from the Behavioral and Brain Sciences* 2019,. 6(1), 3–11.

Fraser, Carol A.(2004). *"Reading Fluency in a Second Language"*. The Canadian Modern Language Review. 61(1), 135-160

Fry, Ron. (2011). *Improve Your Reading*, 6th Edn. New York: Cengage Learning PTR.

Grabe, William and Stoller, Fredricka L. (2011). *Teaching and Researching Reading*, 2nd edn. Great Britain: Pearson Education Limited.

Grabe, William, Yamashita, Junko. (2022). *Reading in a Second Language፡ Moving from Theory to Practice,* Second Edn. Cambridge: Cambridge University Press.

Grellet, F. (1981). *Developing Reading Skills: A Practical Guide to Reading comprehensive Exercise*. Cambridge: Cambridge University Press.

Haladyna, Thomas M. and Michael C. Rodriguez. (2013). *Developing and Validating Test Items*. New York: Taylor & Francis

Harmer, Jeremy. (2011**).** *The Practice of English Language Teaching*,4th edn. Harlow: Pearson Longman.

Heaton, John B. (1989). *Writing Language Tests (Longman Handbooks for Language Teachers)*. London: Longman Group UK Limited.

Hendricks, Kaitlin Mei, "Reading and Test Taking in College English as a Second Language Students" (2013). Psychology Dissertations. Retrieved from https://surface.syr.edu/psy_etd/ 181

Hughes, Arthur. (2003). *Testing for Language Teachers*, (Second edn.) Cambridge: Cambridge University Press.

Klinger, J. K., Vaughn, S., & Boardman, A. (2007). *Teaching Reading Comprehension to Students with Learning Difficulties.* New York: The Guilford Press.

Kong, Jufang. (2019). *Investigating the Role of Test Methods in Testing Reading Comprehension: A Process-Focused Perspective*. Springer Nature Singapore Pte Ltd.

McNamara, Danielle S.(ed.) (2007). *Reading Comprehension Strategies: Theories, Interventions, and Technologies.* New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates, Inc

Mora, J. F., Quito, I. R. and Macías, L. E. (2021). "Reading Comprehension and Reading Speed of University English Language Learners in Ecuador". *Journal of English Language Teaching and Applied Linguistics*, 3(11),11.

Narayanaswamy, K.R. (1975) "The Measurement of Reading Ability". *ELT Journal*, 29(2) 144-147.

Nation, I. S. P. (2009). *Teaching ESL/EFL Reading and Writing.* New York: Routledge.

Nunan, D. (2003). *Practical English Language Teaching.* New York: Mc Graw Hill.

Nuttal, C. (1982).*Teaching Reading Skills*. Cambridge: Cambridge University Press.

**__________**(1996). *Teaching Reading Skills in a Foreign Language*. Oxford: Heinemann.

__________ (2000).Teaching Reading Skills for in a Foreign Language. London: Henemann Educational Books.

Oakhill, J., Cain, K. and Elbro, C. (2015). *Understanding and Teaching Reading Comprehension*. London: Routledge.

Osterlind, S. J. (2002). *Constructing Test Items: Multiple-choice, Constructed-response, Performance and Other Formats*. New York: Kluwer Academic Publishers.

Ostrov, Rick. (2002). *Power Reading: The Best, Fastest, Easiest, Most Effective Course on Speed Reading and Comprehension Ever Developed !* Education Pr.

Pang, E.S., et al. (2003). Teaching Reading. Geneva: International Bureau Educational. http://www.iaoed.org/downloads/prac12e.pdf.

Snow, Catherine. (2002). *Reading for Understanding: Toward an R&D Program in Reading Comprehension*. Santa Monica, CA: Rand Corporation.

Ruddell, M. R. (1999). *Teaching Content Reading and Writing*. New York: John Wiley and Sons Inc.

Sadoski, M. (2004). C*onceptual Foundations of Teaching Reading*. New York: The Guilford Press.

Snowling, M. J., Hulme, C., and Nation, K. editors. (2022). *The Science of Reading: A Handbook*, 2nd edn. NJ: John Wiley & Sons Ltd.

Stavans, Anat and Oded, Brenda. (1993). "Assessing EFL Reading Compherension: The Case of Ethiopian Learners", *System*, 21(4), 481-491.

Wainwright, Gordon (2007). *How to Read Faster and Recall More*...Oxford: How to books Ltd.

Weir,C.J. (1990). *Communicative Language Testing*. London: Prentice - Hall.

Wijaya, M. Sayid. (2018). "Reading Speed Level and Comprehension in Second Language Reading." *Pedagogy Journal of English Language Teaching, 6(1),* 77-*86.*

Williams, E. (1984). *Reading in the Language Classroom*. London: Macmillan Publishing.

Windi, W. Nasriandi N, Syahrir S. (2023). "Reading Skill: Correlation Between Reading Speed and Reading Comprehension." *Journal of Language Teaching and Learning, Linguistics and Literature*, 11(2), 1003-1013.

Yaman, I. & Cakici, D. (2013). "The Effect of Cognitive and Compensation Strategy Instruction on Reading Comprehension Skill." *Journal of Language and Linguistic Studies,* 32(2), 369-384.

# አባሪ አንድ

## የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ

የዚህ ፈተና አላማ የአስረኛ ክፍል በኦሮምኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው። ስለዚህ የሚቀርበውን ምንባብ በተለመደው የንባብ ፍጥነት እና የአነባበብ ዘዴ በመጠቀም አንብቡ።

**መለያ ቁጥር _________**

### ምንባብ አንድ

"የጉለሌው ሰካራም"

"በጉለሌ የነበረው የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማነው?" ብለው ከገፈርሳ እስከ ደጃዝማች ይገዙ ሰፈር ለጠየቁ ሰዎች "ተበጀ! ሰካራሙ ተበጀ! ዶሮ ነጋዴው ተበጀ ነው! ብለው ይነግሯቸዋል። የሕይወቱ ታሪክ ፍፁም ገድል ነው። ጢም ያለው ሽማግሌ ሰው ነው። ራሱን ፀጉር ውሃ ወይም መቀስ ነክቶት አያውቅም። ማለዳ አይናገርም፤ በጠርሙስ የሞላውን ከጠጣ በኋላ ማታ ሲራገም ወይም ሲሳደብ፣ ሲፎክር ወይም ሲያቅራራ ድምፁ ከፈረንጅ ውሻ ድምፅ ይወፍራል። ቢያውቀውም ባያውቀውም ላገኘው ሁሉ ማታ ሰላምታ ይሰጣል። ቢያውቀውም ባያውቀውም ካገኘው ጋር ሁሉ ማታ ይስቃል። የሰላምታው ዓይነት እንደ ወታደር ወይም እንደ ሲቪል ቢሆን ለእርሱ እንደተመቸው ነው። ከሰላምታው ጋር ድምፅ ትሰማለችሁ። ከአፉ ከሚወጣው አንድ ቃል ግን መለየት አትችሉም።

ከሚያሰክር ሁሉ ለመታረም ብዙ ጊዜ አስቦ ነበር። ሰክሮ ያደረበት ሌሊት አልፎ ብርሃን በሆነ ጊዜ " ከእንግዲህ መጠጥ አልቀምስም" እያለ በየቀኑ ምሏል። በነጋታው የበለጠ ጠጥቶ የባሰ ሰክሯል። ለመስከር ይጠጣል፤ ደስ ያለው እንዲመስለው ይጠጣል፤ ብስጭቱን የሚረሳ መስሎት ይጠጣል።

ቡና በተፈላ ጊዜ በጉለሌ በየምድጃው ሥር መልኩን አይተው ያላወቁ ባልቴቶች እንኳ በፍንጃል ቡናን ፉት እያሉ የሌላውን ሰካራም ተረት በተበጀ ላይ እያላከኩ ይሳሳቁ ነበር።

“ይህን መስከርህን ካልተውህ ላንተ ንስሐ አባት አልሆንህም’’ ብለው የመጀመሪያ ንስሐ አባቱ ብዙ ከመከሩት በኋላ መንፈሳዊ ልጅነቱን ከእርግማን ጋር አስወግደውታል። ሠራተኞቹም ለርሱ ተቀጥሮ መሥራትን ከውርደት ቆጥረውት እየነቀፉት ሄደዋል። “መጠጥ ካልተውህ አናገባህም’’ ብለው በየጊዜው ለጋብቻ ጠይቋቸው የነበሩ በቁመናው አሰናብተውታል። በሰንበቴም፣ በማህበርም ማህበርተኛ ለመሆን የጠየቃቸው ነፍሱን ሳይቀር ንቀዋታል።

ብዙ ግዜ ሰክሮ ኦቶሞቢል ሄዶበታል። ሰክሮ በነጋታው ሲነቃ ራሱን እስር ቤት ውስጥ አግኝቶታል። በጉለሌ መንገድ ዳር ባሉት በብዙ የውሃ ጉድጓዶች ሰክሮ ገብቶ የጉለሌ ህዝብ አውጥቶታል። ሰክሮ የጎርፍ ውሃ ከወሰደው በኋላ ብዙ ግዜ የእሳት አደጋ ደርሶለታል። ሰክሮ ከቤቱ መድረስ እያቃተው ከወደቀበት ባቡር መንገድ ሳይነሳ፣ ብዙ ጊዜ በላዩ ላይ ጎርፍ ሲሄድበት አድሯል።

ሰዎች መልካም የሰማእትነት ሥራውን ሁሉ ርካሽ አድርገው ይቆጥሩበታል። በግብረገብ መሰረት አደረግሁት የሚለውን ሁሉ በስካር እንዳደረገው ያናንቁበታል። “በጎ ሥራህን ሁሉ በትኩስ መቃብር ውስጥ አፈር አለበስከው፤ አንተ ሰው ሰው ሁን ሚስት አግባ ልጆች ይኑሩህ’’ ይሉና ይዘልፉት ነበር።

ይህ ሁሉ ውርደትና ርክሰት ነው እንጂ ክብር ከቶ አይደለም። ሁሌም መጥፎ ሱስ ያለበት ሰው ከሰው በታች ነው። ሰዎች ይሸሹታል፤ ፍጹም ወዳጅነቱንና ዝምድናውን አይሹም። እናም ኑሮው በጨለማ እንደተከበበ ይሆናል። የሰካራሙ ተበጀም እጣ ይኸው ነበር።

ምንጭ ከቀድሞ የ10ኛ ክፍል አማርኛ መጽሃፍ የተወሰደ

## መልመጃ ቁጥር ________

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1. የተበጀ ሥራ ምንድነው?

   ሀ. ግብርና   ለ. ዶሮ ነጋዴ   ሐ. ቅቤ ነጋዴ   መ. አናጺ

2. የተበጀ የመጀመሪያው ንስሐ አባት ለምን ከልጅነቱ አሰናበቱት?

   ሀ. የዶሮ ንግዱ ላይ ስለሚያጭበረብር   ሐ. መጠጥ ማቆም ባለመቻሉ

   ለ. ከሰዎች ጋር ሁል ጊዜ ስለሚጣላ   መ. የሐይማኖቱን ትእዛዛት ስለማያከብር

3. ተበጀ ብዙ ግዜ ሰክሮ በላዩ ላይ __________ ሄዶበታል።

   ሀ. ፈረስ   ለ. በቅሎ   ሐ. ኦቶሞቢል   መ. ባቡር

4. ከሚከተሉት ሃሳቦች ውስጥ ስለ ተበጀ ትክክለኛው የቱ ነው?

   ሀ. ተበጀ ብስጭቱን የሚረሳ መስሎት ይጠጣል።

   ለ. ተበጀ መጠጥ የሚጠጣው ከሰፈሩ ድግስ ሲኖር ነው።

   ሐ. የሰፈሩ ባልቴቶች ተበጀን ያደንቁታል።

   መ. ሠራተኞቹ ለርሱ ተቀጥሮ መሥራትን ይፈልጋሉ።

5. ተበጀ ጢም ያለው __________ሰው ነው።

   ሀ. ወጣት   ለ. ሽማግሌ   ሐ. ሀብታም   መ. ደሀ

6. ከሚከተሉት ሃሳቦች ውስጥ ስለ ተበጀ ትክክለኛ **ያልሆነው** የቱ ነው?

   ሀ. ሲፎክር ወይም ሲያቅራራ ድምፁ ከፈረንጅ ውሻ ድምፅ ይወፍራል።

   ለ. ጠዋት ሲነጋ ከእንግዲህ መጠጥ አልቀምስም እያለ በየቀኑ ምሏል።

   ሐ. ማታ ላይ ከአፉ ከሚወጣው አንድ ቃል ግን መለየት አይቻልም።

   መ. ማታ ማታ ሰዎችን ሰላም አይልም።

7. ሴቶች ተበጆን ለማግባት የማይፈቅዱት ለምንድነው?

ሀ. መጠጥ አብዝቶ ስለሚጠጣ ሐ. ለሴቶች ክብር ስለሌለው

ለ. የዶሮ ነጋዴ በመሆኑ መ. ሰዎችን ስለማያከብር

8. የምንባቡ ዋና መልእክት የቱ ነው?

ሀ. የመጠጥ አዝናኝነት

ለ. ተበጆ ሚስት አግብቶ ልጅ መውለድ እንዳለበት

ሐ. መጠጥ በጥቂቱ ቢጠጣ መልካም ነው

መ. ሱሰኛ ሰው በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው ማሳየት

9. ከሚከተሉት ውስጥ ተበጆ መጠጥ የሚጠጣበት ምክንያት ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ለመስከር ለ. ደስ ያለው ለመምሰል ሐ. ከዘመድ ላለመለየት መ. ብስጭቱን ለመርሳት

10. ተበጆ ሰክሮ በነጋታው ሲነቃ ራሱን __________ውስጥ አግኝቶታል።

ሀ. መኪና ለ. እስር ቤት ሐ. ቦይ መ. ሜዳ

11. በጎ ሥራህን ሁሉ በትኩስ መቃብር ውስጥ <u>አፈር አለበስከው</u>። በዚህ አ.ነገር የተሰመረበት ምንን ያመለክታል።

ሀ.መና አስቀረኸው ለ. አፈር በአፈር አደረግከው ሐ. በተንከው መ. መቃብር ውስጥ ገባ

12. ሰዎች መልካም የሰማእትነት ሥራውን ሁሉ <u>ርካሽ</u> አድርገው ይቆጥሩበታል። በዚህ አ.ነገር የተሰመረበት ቃል ተቃራኒ __________ነው።

ሀ. የማይሸጥ ለ. ጥቅም የሌለው ሐ. የማይገዛ መ. ውድ

13. የሕይወቱ ታሪክ ፍፁም <u>ገድል</u> ነው። የተሰመረበት ቃል ተመሳሳዩ __________ ነው።

ሀ. አስገራሚ ለ. ጥፋት ሐ. ልማት መ. ተስማሚ መንገድ

14. የተበጆን ፀጉር መቀስ ነክቶት አያውቅም ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. መቀስ ስለሌለው አስነክቶት አያውቅም ሐ. ፀጉሩን ታጥቦ አይቆረጥም

ለ. ፀጉሩን ተስተካክሎ አያውቅም መ. ፀጉር አስተካካይ ዘንድ ቀርቧል

15. በምንባቡ መሰረት ስለ ሱሰኛ ሰው ትክክል **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. ሱሰኛ ሰው ኑሮው በጨለማ እንደተከበበ ይሆናል

ለ. መጥፎ ሱስ ያለበት ሰው ከሰው በታች ነው

ሐ. ሰዎች ፍጹም ወዳጅነቱንና ዝምድናውን አይሹም

መ. ሱሰኛ ሰው ከሰዎች ጋር ተግባቢ እና ተጫዋች ነው

16. ተበጀ ምን አይነት ሰው ነው?

ሀ.ትዳር የመሰረተ ለ. የጉለሌ ቀበሌ እድር አባል ሐ. በሰካራምነቱ የታወቀ መ. ከሱስ የፀዳ

17. ተበጀ በመጠጥ ሱሰኛነቱ በአካባቢው ማህበረሰብ __________ነበር፡፡

ሀ.የተወደሰ ለ. የተገለለ ሐ.የተወደደ መ.የተረሳ

18.ተበጀን በቁመናው ያሰናበቱት እነማን__________ናቸው፡፡

ሀ. ባለቴቶች ለ. ሰራተኞቹ ሐ. ለጋብቻ የጠየቃቸው ሴቶች መ. መንገደኞቹ

19. በጉለሌ በየምድጃው ሥር ባልቴቶች በፍንጃል__________ ፉት ይሉ ነበር፡፡

ሀ. ወተት ለ. ሻይ ሐ. ቡና መ. ውሃ

20. ነቀፈ የሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ ሊሆን የሚችለው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ዘለፈ ለ.ዘፈነ ሐ.ሸለለ መ. አቅራራ

# አባሪ ሁለት

## የአንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት

የዚህ ፈተና አላማ የአስረኛ ክፍል በኦሮምኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው። ስለዚህ የሚቀርበውን ምንባብ በተለመደው የንባብ ፍጥነት እና የአነባበብ ዘዴ በመጠቀም አንብቡ።

**መለያ ቁጥር _________**

**ምንባብ ሁለት**

## አንድ ገመድ አለኝ

ሁለት ወንድማማቾች እናታቸው ስታርፍ በቤት ውስጥ ያገኙት አንድ ትልቅ ገመድ ብቻ ነበር። ታላቁ ልጅ እጅግ በመበሳጨቱ ገመዱን ጠቅልሎ ጣራ ላይ ወረወረውና ከቤት ወጥቶ ሄደ። ታናሹ ግን ምንም ቢሆን ገመዱ የእናቱ ቅርስ ነውና ጣራ ላይ ወጥቶ አወረደው። ከባዱ ጥያቄ ግን ከዚህ በኋላ ያለውን ኑሮ እንዴት መግፋት ይችላል? የሚለው ነበር። ለብዙ ሰዓታት ተቀምጦ አሰበበት።

ምንም ነገር ሊታየው አልቻለም። አስቦ አስቦ ወደ አንድ ጠቢብ ዘንድ ሄደ። ጠቢቡ ሰው እንዳገኘው የጠየቀው ጥያቄ "ምን አለህ?" የሚል ነበር። መልሱም "ምንም" ጠቢቡ ሰውም "በዓለም ላይ ምንም የሌለው ሰው የለም።" አለው። ልጁ ግን ምንም እንደሌለው ተናገረ።

ጠቢቡም "ይህ ፈጽሞ ሊሆን የማይችል ነው። ረስተኸው ነው እንጂ አንዳች ነገር አለህ" አለው። ጠቢቡም ልጁን ይዞት ወደ አንድ ክፍል ገባ። ክፍሉ ሊዳሰስ በማይችል ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ የተሞላ ነው። ከጠቢቡ ጋር በዚያ ክፍል ውስጥ እንደገቡ "ምን ይታይሃል?" አለና ጠየቀው። ልጁም "ጨለማ አለ" ጠቢቡ ግን እንደገና ጠየቀው። "ሌላ ነገር አለ፤ ፈልገው" ነገር ግን ልጁ ምንም አለ። ጠቢቡም "ና አብረን ቁጭ እንበልና ጊዜ ወስደህ ተመልከት" አለው።

በመካከል ላይም "አሃ" የሚል ድምጽ ከልጁ ሲወጣ ተሰማ። ጠቢቡም "እሺ ምን ተገኘ" አለው። "በዚያ በኩል ባለው ቀዳዳ ብርሃን ነገር ይታየኛል" አለው።

"አሁን አእምሮህን መጠቀም ጀመርክ። ልብ ካላየ ዐይን አያይም ሲባል አልሰማህም። አእምሮውን የሚጠቀም ሰው ሁሉ የሚያየውን ብቻ ሳይሆን የማያውንም ያያል። አእምሮ

ያለው ሰው በሞት መካከል ሕይወት ይታየዋል። መንገድ ያለው ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ ነው። አንተ ውስጥ መንገድ አለ።" ያ ልጅም ማየት ጀመረ።

"እስከዚያ 'የተጠማውን ቁራ ታሪክ' ልንገርህ። ቁራው ውኃ ጠማውና መፈለግ ጀመረ። በመጨረሻም በውኃ ጥም ወደቀ። ነገር ግን ተስፋ ሳይቆርጥ እንደምንም ብሎ ተነሥቶ አካባቢውን ማማተር ጀመረ። በሩቁም አንድ ገንቦ ስላየ እንደምንም ገንቦው ጋ ደረሰ። ሲያይ ጥቂት ውኃ ውስጡ አለ። በአካባቢው ያሉትን ጠጠሮች ገንቦው ውስጥ በመጣል የገንቦውን ታችኛውን ክፍል ድንጋዩ ሞላውና ውኃው ወደ ገንቦው አፍ ደረሰ። ቁራውም ጠጣ።"

በታሪኩ ትረካ መካከል ልጁ አንዳች ቅርጽ ያለው ነገር ተመለከተ። አንዳች የብርሃን መሥመር፤ ቀጭን የብርሃን መሥመር።

"ያ የብርሃን መሥመር ምንድን ነው?" አለው ጠቢቡን።

"ጠጋ ብለህ እየው"

"አትፍራ ጨለማውን ሳትፈራ እንዴት ብርሃኑን ትፈራለህ። ምንጊዜም የማያውቁት ነገር ያስፈራል። ሂድ ተጠጋ።"

ሄደና ተጠጋ፡

"እስኪ ንካው" አለው ጠቢቡ። እየፈራ ነካ አደረገው። ጣውላ ነገር ነው።

"በምትችለው አቅም ሁሉ ግፋው አለው።" ገፋው። ሲጣጣጥ እያለ፤ በመጨረሻ ያ ጣውላ የመሰለ በር ነገር ወደ ኋላው ወደቀ። ያን ጊዜ በውጭ ያለው ብርሃን ፏ ብሎ ገባ። ዓይኑን ጨፈን አድርጎ ሲገልጠው በበሩ ፊት ለፊት ሰፊ መንገድ አለ።

"ሳይነኩት በምኞት ብቻ የሚወገድ ችግር የለም። አየህ ማሰብ የብርሃን ጭላንጭልን አሳየህ። አሁን አይበቃህም"

"ይበቃኛል"

"ታድያስ አሁን ምን አለህ"

"ገመድ አለኝ"

"ሂድ ጊዜ ሰጥተህ አስብ። ይህች ገመድ ሕይወትህን የመለወጫ ምክንያት ትሆንሃለች። ያለበለዚያ ደግሞ የመታነቂያ መሣርያ ትሆንሃለች። ሁለቱም በእጅህ ነው።"

አሰናበተውና ሄደ።

**ከጦማሪ ዲ/ን ዳንኤል ክብረት የተወሰደ ለፈተና እንዲሆን ተስተካክሎ የቀረበ**

## መለያ ቁጥር ________

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1. ከሁለቱ ወንድማማቾች እናታቸው ስታርፍ በቤቱ ውስጥ ያገኙት ምን ነበር?

   ሀ. ትልቅ ገመድ ለ.ትልቅ እንስራ ሐ.ትልቅ ልብስ መ. ትልቅ ማረሻ

2. ታላቅ ወንድምየው ለምን ነበር ገመዱን የወረወረው?

   ሀ. ስለተደሰተ ለ. ስለተበሳጨ ሐ. ሰለመረረው መ. ስላዘነ

3. ልጁ ከተጠማው ቁራ ታሪክ ምን ተማረ?

   ሀ. በሀሳብ መወጠርን ለ. ማስመሰልን ሐ.ተስፋ አለመቁረጥን መ. መጠማትን

4. ታናሹ ልጅ ኑሮውን ለመግፋት መፍትሄ ለማግኘት ወደ __________ ዘንድ ሄደ።

   ሀ. ነጋዴ ለ. ጠቢብ ሐ. ሰፈር ዳኛ መ. ቄስ

5. "በዓለም ላይ ምንም የሌለው ሰው የለም።" የሚለው ምንን ያመለክታል?

   ሀ. ገንዘብ ለ. ምግብ ሐ. መፍትሄ መ. ልብስ

6. ጠቢቡ ልጁን ወደ አንድ ክፍል ሲገባ ክፍሉ በ__________ የተሞላ ነው።

   ሀ. ጨለማ ለ. ቁሳቁስ ሐ. ገንዘብ መ. መፃህፍት

7. "አንተ ውስጥ መንገድ አለ።" በሚለው ሃሳብ መንገድ__________ ያመለክታል።

   ሀ. ጎዳና ለ. መፍትሄ ሐ. መነሻ መ. መድረሻ

8. ገንቦ ውስጥ ምን ነበር?

   ሀ. ማር ለ. ቅቤ ሐ. ውሃ መ. ጠጅ

9. የምንባቡ ዋና መልእክት የቱ ነው?

   ሀ. ገመድን በመጠቀም ወደ መፍትሄ መድረስ እንደሚቻል

   ለ. ማንኛውም ሰው የሚጎዳውና የሚጠቅመው ነገር በራሱ እጅ እንደሆነ ያሳያል

   ሐ. ለውድቀታችን ዋና ምክንያቱ ውጫዊ ነው።

   መ. ሁሉም

10. ጣውላ የመሰለ በር ነገር ወደ ኋላው ከወደቀ በኋላ __________ ታየው።

    ሀ. ጠቢቡ ሰውዬ ለ. ወንድሙ ሐ. ችግሩ መ. ብርሀን

11. ታናሹ ልጅ ገመዱን ያወረደው ከየት ላይ ነው?

    ሀ. ከዛፍ ለ. ከጣሪያ ሐ. ከመስኮት መ. ከቁም ሳጥን

12. አካባቢውን ማማተር ጀመረ ሲል የተሰመተበት ቃል ትርጉም__________ ነው?

ሀ. ማየት  ለ. ገመድ ይዞ መለካት  ሐ. ጥሎ መሄድን  መ. ተስፋ መቁረጥ

13. ልጁ "አሃ" የሚል ቃል ያወጣው ለምን ነበር?

ሀ. ዝምታውን ለመስበር    ሐ. አዲስ ድምፅ በመስማቱ

ለ. ጨለማ ውስጥ በመቀመጡ   መ. ብርሃን ማየቱን ለመናገር

14. አእምሮ ያለው ሰው በሞት መካከል ህይወት ይታየዋል ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. ተስፋ አይቆርጥም  ለ. ስለሞት አያስብም  ሐ. ቢሞትም ይነሳል  መ. ሞትን አይፈራም

15. ቅርስ ለሚለው ቃል ፍቺ የሚሆነው __________ነው፡፡

ሀ. የተከማቸ ልብስ  ለ. ምስል  ሐ. ገንዘብ  መ. የሚወረስ ነገር

16 "አትፍራ ጨለማውን ሳትፈራ እንዴት ብርሃኑን ትፈራለህ፡፡" የሚለው ምንን ያመለክታል?

ሀ. ጨለማን መፍራት እንደማያስፈልግ

ለ. ብርሃን አስፈሪ እንደሆነ

ሐ. ችግርን ሳትፈራ መፍትሄን እንዴት ትፈራለህ

መ. ጨለማና ብርሃንን መፍራት አያስፈልግም

17. …ሲያይ ጥቂት ውኃ ውስጡ አለ፡፡ የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍች________የሚል ነው፡፡

ሀ. ብዙ  ለ. ጎዶሎ  ሐ. ሙሉ  መ. ትንሽ

18. በውጭ ያለው ብርሃን ፏ ብሎ ገባ ሲል የተሰመተበት ቃል ተመሳሳዩ __________ ነው፡፡

ሀ. አነስ  ለ. ጭል ጭል  ሐ. ዘው  መ. ፍንትው

19. ሁለት ወንድማማቾች እናታቸው ስታርፍ በቤት ውስጥ ያገኙት ነገር ነበር፡፡ የተሰመረበት ቃል ትርጉም __________ ነው፡፡

ሀ. ስትተኛ  ለ. ስትሞት  ሐ. ስራ ስትጨርስ  መ. ስትነቃ

20. አሁን አእምሮህን መጠቀም ጀመርክ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. አእምሮህን አባከንከው    ሐ. አእምሮህ ማሰብ ጀመረ

ለ. አእምሮህ ጉዞ ጀመረ    መ. ፍላጎትህን እየገለፅህ ነው

## አባሪ ሶስት

## የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድና ሁለት ዝርዝር መረጃ

## ከ20%

| ከመለያ ኮድ | ፈተና አንድ | ፈተና ሁለት | አማካይ |
|---|---|---|---|
| 1 | 12 | 14 | 13 |
| 2 | 17 | 12 | 14.5 |
| 3 | 9 | 9 | 9 |
| 4 | 13 | 16 | 14.5 |
| 5 | 5 | 9 | 7 |
| 6 | 14 | 13 | 13.5 |
| 7 | 12 | 11 | 11.5 |
| 8 | 5 | 8 | 6.5 |
| 9 | 6 | 8 | 7 |
| 10 | 6 | 2 | 4 |
| 11 | 16 | 20 | 18 |
| 12 | 13 | 12 | 12.5 |
| 13 | 10 | 9 | 9.5 |
| 14 | 12 | 11 | 11.5 |
| 15 | 16 | 17 | 16.5 |
| 16 | 18 | 16 | 17 |
| 17 | 14 | 8 | 11 |
| 18 | 10 | 8 | 9 |
| 19 | 13 | 17 | 15 |
| 20 | 14 | 15 | 14.5 |
| 21 | 17 | 14 | 15.5 |
| 22 | 13 | 15 | 14 |
| 23 | 5 | 10 | 7.5 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 24 | 6 | 8 | 7 |
| 25 | 11 | 16 | 13.5 |
| 26 | 12 | 16 | 14 |
| 27 | 3 | 5 | 4 |
| 28 | 6 | 4 | 5 |
| 29 | 8 | 4 | 6 |
| 30 | 6 | 12 | 9 |
| 31 | 7 | 6 | 6.5 |
| 32 | 4 | 5 | 4.5 |
| 33 | 7 | 8 | 7.5 |
| 34 | 5 | 10 | 7.5 |
| 35 | 6 | 7 | 6.5 |
| 36 | 6 | 8 | 7 |
| 37 | 2 | 5 | 3.5 |
| 38 | 9 | 12 | 10.5 |
| 39 | 13 | 12 | 12.5 |
| 40 | 9 | 7 | 8 |
| 41 | 5 | 8 | 6.5 |
| 42 | 13 | 10 | 11.5 |
| 43 | 11 | 8 | 9.5 |
| 44 | 5 | 11 | 8 |
| 45 | 3 | 9 | 6 |
| 46 | 6 | 6 | 6 |
| 47 | 4 | 2 | 3 |
| 48 | 17 | 14 | 15.5 |
| 49 | 9 | 9 | 9 |
| 50 | 6 | 8 | 7 |
| 51 | 16 | 14 | 15 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 52 | 2 | 3 | 2.5 |
| 53 | 8 | 10 | 9 |
| 54 | 6 | 4 | 5 |
| 55 | 3 | 7 | 5 |
| 56 | 2 | 4 | 3 |
| 57 | 3 | 5 | 4 |
| 58 | 4 | 6 | 5 |
| 59 | 7 | 3 | 5 |
| 60 | 4 | 6 | 5 |
| 61 | 4 | 6 | 5 |
| | ድምር 528 አማካይ 8.66 መ/ልይይት 4. 556626 | 572 አማካይ 9.38 መደበኛ ልይይት 4.255052 | 550 አማካይ 9.02 መ/ልይይት 4.158292 |

# አባሪ አራት

## የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድና ሁለት ዝርዝር መረጃ

| መለያ ኮድ | ፈተና 1 ለማንበብ የፈጀው ጊዜ በሰኮንድ | ፈተና 2 ለማንበብ የፈጀው ጊዜ በሰኮንድ | አማካይ በሴኮንድ |
|---|---|---|---|
| 1 | 311 | 460 | 385.5 |
| 2 | 195 | 246 | 220.5 |
| 3 | 552 | 654 | 603 |
| 4 | 253 | 318 | 285.5 |
| 5 | 329 | 360 | 344.5 |
| 6 | 395 | 540 | 467.5 |
| 7 | 425 | 462 | 443.5 |
| 8 | 303 | 440 | 371.5 |
| 9 | 307 | 410 | 358.5 |
| 10 | 442 | 660 | 551 |
| 11 | 338 | 445 | 391.5 |
| 12 | 295 | 385 | 340 |
| 13 | 316 | 410 | 363 |
| 14 | 355 | 442 | 398.5 |
| 15 | 173 | 245 | 209 |
| 16 | 136 | 172 | 154 |
| 17 | 245 | 395 | 320 |
| 18 | 430 | 526 | 478 |
| 19 | 226 | 252 | 239 |
| 20 | 340 | 460 | 400 |
| 21 | 553 | 660 | 606.5 |
| 22 | 326 | 315 | 320.5 |
| 23 | 551 | 622 | 586.5 |
| 24 | 318 | 540 | 429 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 25 | 401 | 490 | 445.5 |
| 26 | 360 | 480 | 420 |
| 27 | 424 | 552 | 488 |
| 28 | 370 | 542 | 456 |
| 29 | 259 | 440 | 349.5 |
| 30 | 290 | 442 | 366 |
| 31 | 355 | 475 | 415 |
| 32 | 317 | 407 | 362 |
| 33 | 320 | 360 | 340 |
| 34 | 235 | 252 | 243.5 |
| 35 | 300 | 390 | 345 |
| 36 | 542 | 640 | 591 |
| 37 | 395 | 485 | 440 |
| 38 | 603 | 692 | 647.5 |
| 39 | 317 | 342 | 329.5 |
| 40 | 240 | 405 | 322.5 |
| 41 | 600 | 660 | 630 |
| 42 | 558 | 680 | 619 |
| 43 | 554 | 578 | 566 |
| 44 | 240 | 255 | 247.5 |
| 45 | 182 | 400 | 291 |
| 46 | 488 | 670 | 579 |
| 47 | 432 | 500 | 466 |
| 48 | 257 | 347 | 302 |
| 49 | 340 | 400 | 370 |
| 50 | 282 | 420 | 351 |
| 51 | 295 | 358 | 326.5 |
| 52 | 552 | 720 | 636 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 53 | 420 | 604 | 512 |
| 54 | 394 | 600 | 497 |
| 55 | 585 | 680 | 632.5 |
| 56 | 542 | 640 | 591 |
| 57 | 252 | 342 | 297 |
| 58 | 370 | 410 | 390 |
| 59 | 433 | 485 | 459 |
| 60 | 376 | 495 | 435.5 |
| 61 | 398 | 442 | 420 |
| | ድምር 22392<br>አማካኝ<br>367.08<br>መደበኛ ልይይት<br>116.8984 | ድምር 28499<br>አማካይ<br>467.2<br>መደበኛ ልይይት<br>132.5809 | ድምር<br>25445.5<br>አማካይ<br>417.14<br>መደበኛ<br>ልይይት<br>121.8727 |